# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

---

ያለፉት ሦስት ዓመታት አብዮታዊ ትግል
የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታና ተግባሮቻችን

---

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 3 ሐምሌ 1969

## ያለፉት ሦስት ዓመታት ስለ የታዩ ትግል

## የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታና ተግባሮቻችን

"የመጣ በመጣ ግን የየካቲት እንቅስቃሴ ያስገኘው ሊፋቅ ሊደመሰስ የማይችል ዉል አለ:: ይኸውም ሕዝቡ ራሱ ከትግሎቹ የተማረው ትምህርት ነው:: ይህ ትምህርት የወደፊቱን ትግል መንገድ በበቂ አሳይቶዋል:: የወደፊቱ ትግል የሚደረገው ዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ተሰልፎ ጉልታዊ ስርዓቱንና ኢምፔሪያሊዝምን ካገሪቱ ገጸ እንዲያጠፋቸውና አዲስ ሕዝባዊ ስርዓትን እንዲመሠርት ነው:: ጊዜውም እየተቃረበ ሄዱዋል::"

"ታጠቅ ቁጥር ሁለት 1966"

የዛሬ ሁለት ዓመት ተኩል ፈለቀ እውነቱ ከፍ ብለን የጠቀስነውን ቢጽፍ ምናልባት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል በሁለት ዓመታት ውስጥ የዚህን አባባል ትክክለኛነት በገቢር ያረጋግጣል ብሎ አልገመተ ይሆናል::

እንደውነቱ ከሆነ ያሳለፍናቸውን ሶስት ዓመታት መለስ ብለን ስንመለከት፣ በዛን ጊዜ ይህን ያከናወንነውን እርምጃ አስቀድሞ ለመተንበይ አያስደፍርም ነበር:: በነዚህ ሶስት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ የታየውን የለውጥ ማዕበል እንኳን ከበፊቱ ለመገመት ይቅርና ዛሬም አንዳንዶቻችን የለውጡን ፈለግ ለመከተል ፍጥነት የሚጎለን አለን:: በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ አብዮታዊው እንቅስቃሴ አብዮታውያንን ቀድሞአቸዋል::

በየካቲት 1966 ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ከፍተኛ እርምጃ አድርጓዋል:: በጠላቶቹ ላይ የማይናቅ ድሎች ተጎናጽፎዋል:: በዛኑ መጠን "ታጠቅ" ሶስት ዓመት በፊት ለጠቀሰው "የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ተሰልፎ ጉልታዊ ስርዓትንና ኢምፔሪያሊዝምን ካገሪቷ ገጽ እንዲያጠፋቸውና አዲስ ሕዝባዊ ስርዓት እንዲመሰርት" ለሚያደርገው ትግል ጠንካራ መሠረቶች በመጣል ላይ ይገኛል::

በዚህ ጽሑፍ ያለፉትን ሶስት ዓመታት እርምጃዎቻችንና ክንውኖች ለመመርመር፣ አሁን ያለንበትን ሁኔታ ለመጠቆም፣ እንዲሁም ከዚህ በመነሳት የወደፊቱን ተግባራችንን ለመተለም እንሞክራለን:: ይህንና ይህ ሙከራ ቀላል እንደማይሆን እናውቃለን::

ቀላል የማይሆንበትም ምክንያት፣

- 1ኛ በነዚህ በሰባት ዓመታት ውስጥ የተካሄዱት ትግሎች ይዘት ከሚገመተው በላይ ከፍተኛ መሆኑ፣

- 2ኛ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉት ኃይሎች ትግሉ እየገፋ በሄደ ቁጥር ሚናቸውን እየለዩ መሄዳቸው፣ ስለዚህም በየትግሉ ምዕራፍ የተለየ ቦታ ይዘው ስለሚታዩ አረማመዳቸውን በትክክል ማስቀመጥ ማስፈለጉ፣

- 3ኛ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የአብዮታዊ ትግሉን ጉድለትና ምንነት ለመረዳት እያንዳንዱን የትግል ምዕራፍ ለይቶ መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ናቸው::

በሌላ አነጋገር ይህ ጽሑፍ የተፈለገውን ግብ እንዲመታ ከተፈለገ፣ የተወሳሰበውን ሁኔታ ጥርት ባለ መልክ ማቅረብ መቻል ይኖርበታል:: ስለሆነም በኛ በኩል ጉድለት ሊኖር ይችላል:: ይሁንናም አስፈላጊው የትንተና ጥረት ሊገኝ የሚችለው የሁላችንም የሃሳብ መለዋወጥ ሲኖር በመሆኑ አንባቢያን በያሉበት በዚህ ጽሑፍ ላይ ተወያይተው ገንቢ ሃሳቦች ተጨማሪ አስተያየቶች ወዘተ... እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን::

ለማንኛውም ይህ ጽሑፍ ሰባት ዋና ዋና ክፍሎች ይኖሩታል:: በመጀመሪያ የየካቲትን እንቅስቃሴ አመጣጥ ይተነትናል:: በሁለተኛ ደረጃ ከየካቲት ወዲህ የተደረጉት ትግሎችና ያሳለፍናቸውን የትግል ምዕራፎች መርምረን፣ በተለይ ከህዳር 1968 ወዲህ ያለውን ሁኔታ በመተንተን የያንዳንዱን የሕብረተሰብ ክፍል ሚናና የሚናውን አረማመድ እንዲሁም የደረስንበትን የትግል ደረጃ ለመጠቆም እንሞክራለን:: ሰባተኛው ክፍል የሚያተኩረው በተግባራችን ላይ ይሆናል::

## I. የየካቲት አንቅስቃሴ መሠረታዊ ምክንያቶችና

### የአንቅስቃሴው ታሪካዊ ፍቺ

በየካቲት ወር 1966 ሰፊ ሕዝባዊ አብዮታዊ አንቅስቃሴ በአገር አቀፍ ደረጃ ተነሳስቶ ኢትዮጵያን አጥለቀለቃት::

በየካቲት 1966 የፈነዳው አንቅስቃሴ ይኸው ዛሬ የደረስንበትን የትግል ደረጃ ባዲስ መልክ የጀመረ አንቅስቃሴ ነበር::

እንደማናቸውም ከፍተኛ የትግል ምዕራፍ የካቲት በተራማጆች ዘንድ በብዙ ክርክር አስከትለዋል::

በዚህ አንቅስቃሴ ባቢያ በፀረ ኃይለ ሥላሴ መድረክ የተሰበሰበው "ተራማጅ" መልክ መልኩን ይዞ ወጥተዋል:: የካቲት 1966 ስንዴው ከአንክርዳዱ መለየት የጀመረበት ታሪካዊ የትግል ወቅት ነበር::

በዚን ወቅት ተራማጆች በተሰበሰቡባቸው ወይም በተደራጁባቸው መድረኮች ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ ውይይቶች የኃሳብ ልዩነቶች ከዚያም አለፍ የመስመር ትግሎች ተካሂደዋል:: የአንቅስቃሴውን ምክንያቶች ጠባዩን ጉድለቱንና አዝማሚያውን እንዲሁም የጊዜውን የተራማጆች ተግባር በሚመለከት ነጥቦች አከባቢ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰነዘሩ ነበር::

በዚን ጊዜ ውዥንብር ውስጥ ይዋዥቅ የነበረው ክንፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከተጨባጩ ሁኔታ እየራቀ ከመደብ ጥቅሙ ጋር ተያይዞ ወደ ፀረ አብዮት ሰፈር ሲጠልቅ ታይተዋል:: ዛሬም አዝማሚያውን በመቀጠል ላይ ነው::

በዚን ጊዜ ጥረት ያለው ግምት የሰጠው ክፍል የሕዝብን ድጋፍ ተከታይነት እያገኘ ለሰፊው ሕዝብ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ ትክክለኛ አመራር እየሰጠ መተዋል::

ከዚህም በመነሳት ጊዜያዊ የኢትዮጵያ ሁኔታን ለመረዳት ምን ያህል ስለ የካቲቱ አንቅስቃሴ ትክክለኛ ግምትን እንደሚጠይቅ ለመረዳት አያዳግትም:: ያንኑ ያህል የኢትዮጵያን ሕዝቦች የነፃነት ትግል አጣሞ ለማቅረብ የተነሱ ኃይሎች ከሁሉ አስቀድመው የየካቲትን አንቅስቃሴ አጣመው በማቅረብ እንደሚጀምሩ የማይታበል ሃቅ ነው::



ለዚህም ነው ጸሑፋችንን የየካቲትን አንቅስቃሴ መሠረታዊ ምክንያቶችና ታሪካዊ ፍቺውን በመመርመር የምንጀምረው:: ከዚህም ተነስተን ለሚቀጥለው ክፍል ማለትም ጊዜያዊ የኢትዮጵያ ሁኔታን ትንተና ከስረ መሰረቱ ለገረዳ እንችላለን ብለን እናምናለን::

### የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ መሠረታዊ ቅራኔ፣ ጠባዩና ውጤቱ

ከፍ ብለን የጠቀስነው ታጠቅ የመጀመሪያ አረፍተ ነገር የሚቀጥለው ነበር:: "ያንዱን ሕብረተሰብ የውስጥ ትግሎችና ከዚህም ትግሎች የሚፈልቀውን የወደፊት ገስጋሴ የሚወስነው ኃይለ ሕብረተሰቡ የሚቆምበት የኢኮኖሚ ስርዓት ነው":: ባጠቃላይ ደረጃ ስንመለከተው ተደጋግሞ እንደተነገረው፣ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የኢኮኖሚ ስርዓት ከፊል ባላባታዊ ከፊል ከሉኒያል ነው:: ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ቅራኔ በዚህ ስርዓት በሚጠቀሙ በዚህ ስርዓት በሚበዘበዙት ማሀል ይሆናል:: ይህም ማለት ደግሞ ባንድ በኩል ባላባታዊ መደብ ኢምፔሪያሊስቶችና ቢሮክራቲክ ከበርቴው በሌላ በኩል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞትና የሽረት ቅራኔ ውስጥ ይገኛሉ ማለት እንጂ ሌላ ምንም ማለት አይደለም::

ይሁንና ያንዱን ሕብረተሰብ ቅራኔ ከሕብረተሰቡ እርምጃና ከእድገት ደረጃው ነጥለን ልናየው አንችልምና ከዚህ ቅራኔ ብቻ በመነሳት በምንም ዓይነት የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ምንነት ለገረዳ አንችልም:: በየካቲት ዋዜማ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የደረሰበትን ደረጃ፣ የተከተለውን አረማመዱ መመልከት ይኖርብናል:: ከዚያም በመነሳት የሕብረተሰቡ መሠረታዊ ቅራኔ ዋነኛ ይዘት የትኛው እንደሆነ ለገረዳ እንችላለን::

ኢትዮጵያ ለተወሰኑ ዓመታት ንፁህ ባላባታዊ ስርዓት የሰፈነባት አገር ነበረች:: ኢኮኖሚዋም ባላባታዊ ነበር:: እንደማንኛውም ሕብረተሰብ የኢትዮጵያም ሕብረተሰብ የተወሰነ እድገት ተከትለዋል:: የባላባቱ ስርዓት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ጊዜ በርባታ ኃይሎች በርባታ ግንኙነት ማሀል ቅራኔ እንደመፈጠሩ ሁሉ፣ በባላባታዊው ስርዓት ስር የካፒታሊስት የርባታ ግንኙነት መፀነሱ አልቀረም:: ይሁንና ካለው የዓለም ዓቀፍ ሁኔታ ሲታይ ይህ እድገት ጤናማ በሆነ መንገድ ሳይከናወን ቀርቷል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ ማንኛውም የአፍሪካ አገር ኢትዮጵያ ከኢምፔሪያሊስቶች የወረራ ሙከራ አላመለጠችም:: ግን ደግሞ ኢትዮጵያ ለረዥም አመታት ይህንን ወረራ ለመቋቋም ችላለች:: ይህ ወረራ በተለየ መልክ በኢትዮጵያ የገባው በሌሎች አፍሪካ አገሮች አንፃር ሲታይ በጣም በቅርብ ጊዜ ነው:: በኢትዮጵያ ኢምፔሪያሊስቶች በሰረፉበት ጊዜም፣ ለካፒታሊስት የርባታ ግንኙነት በር ከፍተዋል::

ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ከባላባታዊ ስርዓት ወደ ከፊል ባላባታዊ ከፊል ካፒታሊስት ስርዓት አለፈል ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በተለይ ባለፉት አመታት፣ በኢምፔሪያሊስቶቸ ባገራቸን መደላደልና የካፒታሊስት የርባታ ግንኙነት ማስገባት፣ እንዲሁም ደግሞ ከራሱ ከሕብረተሰቡ እድገት የተነሣ፣ ባለመጠነ የእድገት ደረጃ ቢሆንም የካፒታሊስት ስልተ ምርት ባገሪትዋ ምጣኔ ኃብት ውስጥ ሰርጎ ገብቶዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት፣ ሁለት መሰረታዊ ሃቆች ልንረዳ ይገባል፡፡

1ኛ— ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ከፊል ባላባታዊ ከፊል ከሎኒያል ቢሆንም በዚህም አንፃር ኢኮኖሚዋ ከፊል ባላባታዊ ከፊል ካፒታሊስት ቢሆንም፣ ባላባታዊው ኢኮኖሚ ዋናው / ዶሚነንት / ሆኖ ቆይቷል፡፡

2ኛ— ምንም እንኳ ጤናማ ባልሆነና ባለመጠነ የእድገት ደረጃ ቢሆንም ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ እስከ ተወሰነ ደረጃ /እንመለከበታለን/ ተስፋፍቷል፡፡

እንግዲህ በየካቲት የዘውዱ ሥልጣን የወበጡት መደቦች የቆሙለት ስርዓት ፍፁም የበሰበሰ ከመሆኑም በላይ በታሪክ አንፃር ሲታይ ወደ ኋላ የቀረ ነበር፡፡ ያለውን የሕብረተሰብ እድገት እፍኝ ከመያዙም በላይ ሰፊውን አምራች ሕዝብ ከምርቱ ነጥሎ በጥቂት ሰዎች ምቾት ላይ የተመሰረተ ስርዓት ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ምናልባት ከማንኛውም አገር በላይ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ የከረረ ቅራኔ ውስጥ ከተታል፡፡ ከሰፊው ገበሬ አንስቶ እስከ ወዛደሩ እንዲሁም ንዑስ ከበርቴውን ካለው ስርዓት ጋር ተፃራሪ ቅራኔ ውስጥ ከተታል፡፡ ለተዘረዘሩት መደቦች ያለው ስርዓት ፍፁም ተስማሚ ባለመሆኑ እነዚህ መደቦች የስርዓቱን መተካት እንደፈለጉ አያጠራጥርም፡፡ ይህ ሁኔታ ለየካቲት እንቅስቃሴ መነሳት መሰረታዊ ምክንያቶች ከሆኑት አንደኛው ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ከእንቅስቃሴው የፈለቀውን የትግል ግስጋሴ የወሰነው ይህ መሠረታዊ ሃቅ ነው፡፡

ይሁንና የየካቲት እንቅስቃሴ መነሳት ከዛም ለበሰት ዓመታት መሆኑ ነው፣ ተፋፍሞ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ መድረስ ከዚህ ከቅራኔ መክረር ብቻ የተወሰነ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የየካቲትን እንቅስቃሴ ልዩ ያደረገው፣ እንቅስቃሴው አገር አቀፍ ሊሆን መቻሉና የተጨቆኑ መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ባንድነት ሊነሱ መቻላቸው ነው፡፡



ለእንቅስቃሴው መፈንዳትና ከፍተኛ ጥልቀት ባለው ማዕበል መቀጠል የባላባቱ ስርዓት ዋናው የኢኮኖሚ ስርዓት መሆኑ ምክንያት የሆነውን ያህል፣ ለእንቅስቃሴው አገር አቀፍ መሆን የካፒታሊዝም አርባታ ግንኙነት እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ማደጉ ምክንያት ሆኖታል፡፡ ቅድመ የካቲት ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የተበታተኑ በየጊዜው የሕብረተሰቡን አንዱ ክፍል ብቻ ያስነሱ ንቅናቄዎች ነበሩ፡፡ በየካቲት ዋዜማ ግን በኢትዮጵያ የተስፋፋው የካፒታሊስት የርባታ ግንኙነት አገሪትዋን እንደ ሸረሪት ድር ያስተሳሰራት የኢኮኖሚ መዋቅር እንዲኖር በማድረጉ የየካቲት እንቅስቃሴ አገር አቀፍ ሊሆን ቻለዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለየካቲት እንቅስቃሴ ሌላኛው መሠረታዊ ምክንያት ነው፡፡

በነዚህ ሁኔታዎች ላይ የ1965 ቱን ረሃብ፣ የዋጋ መወደድ፣ ወዘተ... የመሳሰሉ ጊዜያዊ ምክንያቶች ተደምረው ይህ ታሪካዊ አብዮታዊ ንቅናቄ ተነሣ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግልም በዚሁ ባቢያ አዲስ ምዕራፍ ውስጥ ሊገባ ቻለዋል፡፡

በተለይ ዛሬ ወደ ኋላ መለስ ብለን ያለፉትን ዓመታት ስንመለከት የካቲት 1966 ዓይነተኛ ምርዕና ለመሆኑ የማያጠራጥሩ ሃቆች እንገነዘባለን፡፡ የቢሮክራቲክ ከበርቴውና የባላባቱ የህብረት በገዢነት ስከፊል ወደ ተቃዋሚነት ያለፈበት፣ ታፍኖ የቆየው የጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ፍላጎት የሚገፋፉበት መድረክ ያገኘበት፣ ሕዝቦች በየረድፉ የትግል አርማቸውን የዘረጉበት ታሪካዊ ወቅት አለ ቢባል፣ ኢትዮጵያን በሚመለከተው በኩል ይህ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ስለዚህም የሕዝቡ ትግል አዲስ ወለል ይዞ ቀርቦአል፡፡ ገበሬው ለመሬቱ ያደረገውና የሚያደርገው ትግል ጨባጭ ውጤት በማግኘት ላይ ነው፡፡
የወዛደሩም መደብ ለመጀመሪያ ጊዜ በፖለቲካው መድረክ እንደ አንድ መደብ ተከሰቷል፡፡ የመደቡን ሕብረተሰባዊ ርዕዮተ ዓለም በማግኘት ላይ ነው፡፡ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች በፖለቲካው ትግል በቀጥታ በመሰለፍ፣ ከወዛደሩ እንቅስቃሴው ጋር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመዋሃድ የወዛደሩን ግንባር ቀደም ድርጅት ወደ መመሥረቱ እየተቃረቡ ነው፡፡
ለነዚህ ሁሉ ዓይነተኛ አርዓያዎች / ቢሊታቢ ቸንቡስ /
መነሻ ሆነዋልና የየካቲት 1966 እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ብሔራዊ ዲሞክራቲክና ሕዝባዊ ትግል ታሪካዊ ቦታ አለው እንላለን፡፡

## II. ከየካቲት ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል አረማመድ

ከዋና ዋና ደርጊቶች ዝርዝር ለመረዳት እንደምንችለው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ባጠቃላይ ደረጃ ከፍተኛ እርምጃ አድርጓል ማለት ቢቻልም ቅሉ፣ በዝርዝር ሲታይ የገነፈለበት የቀዘቀዘበት፣ የተጨናከረበት የተሳከመበት ጊዜ አለ:: ይህንንም መረዳት ለማገናዘብም ትንተና ከፍተኛ ትርጉም አለው:: የያንዳንዱን ደርጊት ትርጉም በትክክል ለመረዳት ስለሚጠቅም፣ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያልተያያዙ ግምቶችን ከመውሰድ ያስቆጥበናል:: እንዲሁም በፖለቲካ መድረክ ውስጥ የሚታዩትን ኃይሎች ትክክለኛ ጠባይና አረማመድ ለመረዳት ይጠቅማል::

እዚህ ላይ ከመጀመሪያው ማስቀመጥ ያለብን አንድ ሃቅ አለ:: ይህም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ያስተማረንና የተሰፍንለት ውስብስብ ተጋድሎ የጣለብን አደራ ነው:: ከዚህም አደራ ተነስተን የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግልና ጊዜያዊ ሁኔታን በምንመረምርበት ጊዜ በተቻለ መጠን ከነባራዊው ሁኔታ መነሳት ይኖርብናል:: በዛሬ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል እርምጃ አለማሰየት በትግል ውጤታችን ተጠቅመን ወደፊት አንራመድ ማለት ነው:: ያንኑ ያህል የሰፊውን ሕዝብ ጉድለቶች አለመጠቆም ወላላ ወይም አወደድ ባይነት እንጂ ፀኑ የሕዝብ ወገኛ መሆን አይደለም:: በፖለቲካው መድረክ የተሰለፉትን ኃይሎች ምንነት በምንገልፅበት ጊዜ እንደዚሁ ትንተናችን በሃቅ ላይ መመስረት አለብን:: የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል የሚጫወተውን ሚና በንመረምር ጠቃሚውን በጠቃሚነቱ አጥፊውን ባጥፊነቱ ልናየው ይገባል:: ካለበለዚያ ግን የምንሰጠው ግምት ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከራሳችን ግላዊ ግምት የመነጨ ይሆናል::

እንግዲህ በነዚህ ነጥቦች ከተስማማን ዘንዳ ባለፉት ሰባት ዓመታት በተከናወነው እንቅስቃሴ ምርመራ ላይ እንሰማራ:: ባጠቃላይ ደረጃ በአምስት ወቅቶች ላይ እናተኩራለን::

1ኛ ከየካቲት እስከ አማን አንዶም ከስልጣን መውረድ፣ 2ኛ ከአማን አንዶም መውረድ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ 3ኛ ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እስከ አዋጁ መነሳት፣ 4ኛ ከአዋጁ መነሳትና ከብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም እስከ ተፈሪ ባንቴ የመንፈንቀለ መንግሥት ሙከራ፣ 5ኛ በተፈሪ ባንቴ የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ ወዲህ::



## 1. ከየካቲት እስከ አማን አንዶም መውረድ

በየካቲት 1966 ከፍ ብለን የተመለከትነው እንቅስቃሴ ፈነዳ:: መሠረታዊ ምክንያቶቹ የትኞቹ እንደሆኑ አይተናል:: ታሪካዊነቱም ከምን የተነሳ መሆኑን ጠቅሰን አልፈናል:: አሁን እንግዲህ ይህ ንቅናቄ ወዳስከተለው ውጤት እናልፋለን::

የየካቲት እንቅስቃሴ በፈነዳበት ሰዓት የሃይለ ሥላሴ መንግሥት ንቅናቄውን በቀላሉ ሊገታ የቻለ መስሎት ነበር:: በምንም ዓይነት ሁኔታ እንኳን ሃይለ ሥላሴ ይቅርና ተራማጅ ኃይሎች እንኳ ስር ነቀል እንቅስቃሴ አላጠበቁም ነበር:: ይህ ሆኖ ሳለ፣ እንቅስቃሴው በገፋ ቁጥር መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቀን ወደ ቀን እየተነሳሳ የደረሸውን ማሰማት በጀመረበት ሰዓት ገዢውን መደብ ከጠበር ላይ የጣለውን ያህል ተራማጆችን አዋከበአቸዋል:: ሃይለ ሥላሴ በዚን ሰዓት በመጀመሪያ እንቅስቃሴውን በሃይል ለመግታት ሞክሮዋል:: ከዛም አዝማሚያውን ሲያየው አንዳንድ ለውጦች ማድረግን መረጠ:: የተወሰኑ ቅናሾችን ዋጋ በማስቀነስ በኃይል ያቃተውን አብዮታዊ ማዕበል በሌላ ሊገታው ሞከረ:: ይህ ሁሉ ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም:: የሚቀጥለው እርምጃ የነበረውን የነአክሊሉን ካቢኔ መተካት ነበር:: ለዚህም ጊዜውን ይጠብቅ የነበረው የነእንዳልካቸው ቡድን ራሱን አቀረበ:: እንዳልካቸው ባንድ በኩል በተለይ የወታደሩን ክፍል እንቅስቃሴ ለመግታት ከወታደሩ ማሀል ልዩ ከሚቴ በማቋቋም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ላይ የፀረ አብዮትን ሰይፍ ሰመዘ፣ በሌላ በኩል የለውጥ ሃዋርያ ሆኖ ለመቅረብ ሞክሮ ነበር፣ ሆኖም ግን አልተሳካለትም:: ይህ ሁሉ በሆነበት ሰዓት የፀረ አብዮት ኃይሎች በየጊዜው ተበፋ አደርገው ነበር:: ይህ ተበፋ ኢምፔሪያሊስቶችንም ይመለከታል:: በዚሁ መጠን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ትግሉን እያከረረ የጥያቄዎቹን ይዘት እያጠናከረ መተዋል:: በተለይ የትግሉ ዋነኛ ኢላማ የፋሽስታዊው የሃይለ ሥላሴ መንግሥት ከስልጣን መውረድ ነበር::

የዚህን ወቅት ዝርዝር ትንተና ሌሎች የማህበራችን መጽሔቶች በሰፊው ስለተነተኑት በዚህ ነጥብ ላይ መመላለስ መደጋገም ይሆናል:: ስለዚህስ የንቅናቄውን ዋና ዋና ይዘት በመጠቆም እንወሰናለን:: ሁለት ነጥቦች እናንሳ::

አንደኛ፣ በገዢው መደብ ዘንድ ይህ ሁሉ የቀለበጣ ሙከራ ሲደረግ፣ ይህ ሁሉ ሹም ሽር ሲከናወን፣ የተወሰኑ የገዢው መደብ ክፍሎች ለምሳሌ ከስልጣን የተባረረው ቡድንና አጫፋሪዎቹ ይበሳጩ እንጂ፣ መደቡ ባጠቃላይ ሲታይ ምናልባት አዝማሚያውን ሲያዩት ፍራቻ ይደርባቸው እንጂ መሠረታዊ የመደብ ጥቅማቸው አልተነካም:: አለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም፣ በተለይ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣ ንቅናቄውን ለመግታት በየቦታው ኃይሎችን ያስተባብር እንጂ የተደረገውን የቡድን መለወጥ በክፋ አይኑ አልተመለከተውም::

ለዚህ በዛን ዘመን የኢምፔሪያሊስቶችን ጋዜጦች መመልከት ይጠቅማል::

ሁለተኛው ሰፊውን ሕዝብ በማመለከተው በኩል ተራማጆች በእንቅስቃሴው መቀደማቸውን በሚገባ ተረድተዋል:: ይሁንና ከፍተኛ ዝቡፋና የትግል ፍላጎት ባያዳብርባቸው አልቀረም:: ሰፊው ሕዝብም በትግሉ ወሳፈኝ ተይዞ የቻለውን ያህል ታፍኖ የነበረውን ቅሬታውና ለመንግሥቱ ያላቸውን ጥላቻ አሰምተዋል:: ይሁንናም የትግሉ የመጨረሻ ውጤት በግልጽ አልታየም:: በተለይ በእንቅስቃሴው የተሳተፈው የወታደር ክፍል፣ በዛን ጊዜ የነበረውን ኃይል አልተረዳም ነበር:: ምናልባትም ወታደሩን በጠቅላላ ለማስተባበርና በተወሰነ ዓላማ ስር ለማሰለፍ ቀላል አልነበረም ይሆናል:: ዓላማም የነበራቸው ወታደሮች ይህ የማስተባበሩ ጥያቄ ከችሎታቸው ውጭ የነበረ ሆኖ ታይቷቸው ይሆናል:: የሆነው ሆኖ በኃይላቸው ለመጠቀም ብዙ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል:: ብናስታውስ ሃይለ ሥላሴን በመንግሥት ደረጃ ወታደሩ የተካው የካቲት በተነሳ በስምንተኛው ወር ነው::

እንግዲህ ከፍ ብለን የጠቀስነው የገጠሩ መደብ በጋት በይበልጥ እየጠነከረ የመጣው፣ በሌላ አነጋገር አድሃሪው "ነገር ተበላሸ" ማለት የጀመረው፣ እንዳልካቸውም ከተወገደ በኋላ ባለስልጣን ማሰሩ፣ የባለሥልጣኖቹን የገንዘብ ምንጭ ማጣራቱ በይበልጥ እየከረረ በመጣበት ጊዜ ነው:: ያም ቢሆን ግን ገጠሩ መደብ በስጋት በስተቀር የተጨበጠ የመደብ ጥቃት አልደረሰበትም:: አድሃሪው የመጀመሪያውን ጥፊ የተቀበለው በማያጠራጥር ሁኔታ መስከረም 2 1967 ዓ.ም. ነው:: ያቺን እንቅጥቃጭ እስከ ጊዜው አይረሳትም:: ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም የመጀመሪያውን ከፍተኛ የፖለቲካ ድል የተቀዳጀው በዚሁ ቀን ነበር::

መስከረም ሁለት እውነትም ከፍተኛ የፖለቲካ ድል ነው:: ያገሪቱየ ከፍተኛ ስልጣን በዛን ለት የቀደሞ ገዥ መደቦችን አምልጧቸዋል:: ይሁንናም ግን መስከረም ሁለት በዛኑ መጠን የረጅም ትግል አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት እለት ነበር:: ፀረ አብዮት በዛን ቀን የመጀመሪያውን ውጊያ ድል ተመታ:: ሰፊው ሕዝብም የመጀመሪያውን ውጊያ ድል ተቀዳጀ:: በፀረ አብዮትና በሰፊው ሕዝብ ማህል የሚካሄደው ጠርነት ግን ገና መጀመሩ ነበር::

ከዛን እለት ወዲህ የፀረ አብዮት ኃይሎች የትግል አርማ ያተኮረው፣ አዲሱን ስልጣን መካፈል ላይ ፣ ከተቻለም በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ነው:: እንዲያውነቱ ከሆነ ለዚህ ዓላማው የፀረ አብዮት ኃይል ችሎታ ነበረው:: በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት ፀረ ሕዝብ መደቦች በኃይላቸው በሚገባ ተጠቅመውበት ኃይል በሳሉ በበሩ ሲበረርባቸው፣ ሁኔታው ቢያባዝናቸውም፣ አማን አንዶምን በመስከት ሲያስገቡ ችለዋል:: እንደውነቱ ከሆነ አማን አንዶምን በስልጣን ላይ ባስቀመጡበት ጊዜ የመደባቸው አጠቃላይ ጥቅም አሁንም ሊውልላቸው መቻሉን ተረድተዋል::



በተለይ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በአማን አንዶም ላይ ከፍተኛ ተስፋ ጥሎበት ነበር:: አማን አንዶም የኢትዮጵያው ናስር "የኢትዮጵያ መድህን" የተባለለት ሰው ነው::

በዚህም ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይ የኢትዮጵያ ተራማጆች የመጀመሪያውን ውጊያ ቢያሸንፉም ጠርነቱን ለማሸነፍ ገና ብዙ ትግል እንደሚቀራቸው ተረድተዋል::

ከመስከረም ሁለት በኋላ አማን አንዶም የደርጉ ሊቀመንበር ሆኖ ይሾም እንጂ በደርጉ ውስጥ የሱ ተፃራሪ ኃይሎች ነበረ ከመደብ አንፃር እንኳ ቢታይ ደርጉ በብዛት ከንዑስ ከበርቴው ክፍል ከመነጩ ወታደሮች የፈለቀ ቢሆን አብዛኛውም "በፍልስፍና" ደረጃ "ኢትዮጵያ ትቅደምን" የተቀበለ ነበር:: በሃገራችን ላይ የዛሬ አርባ ዓመት ሂትለር "ጀርመን ትቅደም" ብሎ ነበርና ዛሬ "ኢትዮጵያ ትቅደም" ማለት ፋሺዝም ነው የሚለውን ረቂቅ የመደብ ትንተና ወደጎን መተው ልንገደው ነው::

ሆኖም ቀረ "ኢትዮጵያ ትቅደም" ማርክሲያዊ ሌኒናዊ መመሪያ አይደለም ብለን አገር ወዳዱ መመሪያነቱን ልንነፍገው አይገባም:: ዛሬ ማንም ማርክሲስት ኢትዮጵያ ወደ ኋላ ትቅር ብሎ የሚታገል የለም::

ለማንኛውም በኢትዮጵያ ትቅደም አገር ወዳዱ መመሪያ አማን አንዶምን የሚፃረሩ ኃይሎች በደርጉ ውስጥ ነበሩ ብለናል:: በነዚህ ኃይሎችና በአማን አንዶም ማህል የነበረው ቅራኔ ያለ ምንም ጥርጥር ተፃራሪ ነበር:: ከፍ ብለን እንዳልነው ቀደሞ ገዥ መደብ ዓላማ ከንዑስ ከበርቴው ሥልጣን መካፈል፣ ቢቻልም ጠቅላላውን መቆጣጠር ስለነበር፣ አማን አንዶም ጊዜውን ጠብቆ ደርጉን ለመደምሰስ እንደፈለገ የታወቀ ነበር:: የተባለውም አልቀረም፣ ሆኖም ግን አማን አንዶም ሳይሳካለት ቀርቶ ከ60 የቀደሞ ባለስልጣኖች ጋር ተረሸነ :: በአገሪቱ አመራር ላይ ወታደራዊው የንዑስ ከበርቴ ክፍል አመራሩን አጠናከረ:: ከእንግዲህ በዚህ በንዑስ ከበርቴ መደብና በገዥው መደብ ባለው ቅራኔ በዚሁ መንግሥትና በሰፊው ሕዝብ ባለው ቅራኔ በመነሳት ያገራችን የፖለቲካ ኃይሎች ልዩ ልዩ ሚና ሲጫወቱ ታይቷል::

ይህ ሁሉ ቢሆን ግን ሰፊው ሕዝብ ወደር በሌለው መልክ በየካቲት እንደተነሳው ሁሉ ትግሉን ቀጥለዋል:: ይሁንና በየካቲትም የነበሩት ጉድለቶች የግንባር ቀደም ድርጅት ጉድለት የአብዮቱ ሃይሎችን ያስተባብር ድርጅት አለመኖር ወዘተ...አልተወገደም ነበር:: ተራማጆች በየፊናቸው የተደራጁባቸውን ቡድኖች ለማጠናከር በማህላቸውም አንድነት ለመመስረት ጥረት ሲያደርጉ ባላቸውም ኃይል በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ታይተዋል:: ለጊዜውም ትክክለና የትግል መመሪያዎች የሰነዘሩ ነበሩ::

ከማህላቸውም ፍፁም ስህተተኛና ተገቢ ያልሆኑ አስፈሪ መፈክሮች የሰነዘሩ ነበሩ:: የተወሰነው የንዑስ ከበርቴ ክፍል በወዘደረም ሰዎ ሆነ በሌላ ባለስልጣን የመጠበቅ ኃይልና ፍላጎት ስለነበረው ባጠቃላይ የተነሳው "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ይቋቋም በሚለው ስር ሲሆን ከዚህም መፈክር በመነሳት ይህናው የንዑስ ከበርቴ ክፍል ደርጉን ፈቶ በሉ ለማለት "ፋሺስት" የሚለውን ትንተና ማቅረብ ነበረበት:: ይህም ከተጨባጭ ሁኔታ ሳይሆን ከግል ፍላጎት የመነጨ ግምት ነበር:: ስለሆነም ይህ ቡድን ይህን መፈክር ከጨበጠ ወዲህ በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች ምንነት በደርጉ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች የደርጉን የመደብ ጠባይ እንዲሁም የነዚህ ቅራኔዎች ውጤት የሆኑትን ተራማጅ አዋጆች ምንነት ካለመረዳት በፖለቲካው መድረክ በቀረቡት ዋና ዋና ጥያቄዎች ላይ ጠቅላላ ውዥንብር ውስጥ ገብተዋል:: ከጊዜ ወደ ጊዜም የተንተነው ፀረ ሕዝብነት የፀረ አብዮት ኃይሎችን በዙሪያው ሰበሰበለታል::

ወደ ተነሳንበት አርዕስት ለመመለስ ያህል አማን አንዶም በተገደለበት ጊዜ አብረውት መፈንቅለ መንግሥት ለመጠንሰስ የሞከሩት 60 የቀድሞ ባለስልጣኖች ተገደሉ:: ይህም የቀድሞ ገዢ መደቦችና ኢምፔሪያሊስቶች ተስፋቸውን የጣሉበት ሰው ከስልጣን የተገለለበት ቀን ስለነበር ለሰፊው ሕዝብ ሌላ ተጨማሪ ድል ነበር:: ለቀድሞ ገዢ መደቦችና ኢምፔሪያሊስቶች ግን ሁለተኛ ውርደት ነበር:: ለዚህም ነው አንድ አድሀሪ የእንግሊዝ ጋዜጠኛ ስለ ኢትዮጵያ መጽሐፍ ጽፎ አርስቱን "ጭንቅላታን ሁለት ጊዜ የቀነጠሰች አገር" ብሎ ያለው:: አንደኛው ሃይለ ሥላሴ ቢሆን ሁለተኛው አማን አንዶም መሆኑ ነው:: እናም ወደ ሁለተኛው አርእስት እናልፋለን::

## 2. ከአማን አንዶም መውረድ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

እንግዲህ ባጠቃላይ ደረጃ አማን አንዶም ለፀረ አብዮቱ ክፍል ምን ያህል "ተስፋ" ሆኖ እንደነበር ከሞላ ጎደል አይተናል:: የሱ ከስልጣን መገለል ከዚያም አልፎ መገደሉ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድ ድል እንደነበርም አይተናል:: ዋናው የአማን አንዶም መገደል ውጤት ግን በአገሪትዋ ከፍተኛ ስልጣን ደረጃ ወታደራዊውን የንዑስ ከበርቴ ክፍል ማጠናከሩ ነው:: ለዚህም ከአማን በኋላ የተካሄዱት ድርጊቶች ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው::

የሆነው ሆኖ አማን አንዶም በስልጣን ላይ እስከነበረበት ሰዓት፣ በሰፊው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ የትግል መንፈስ ቢኖርም ምናልባት ሃይለ ሥላሴ ከስልጣን ከመወገዱ ሌላ፣ በተለይ በኢኮኖሚ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሠረታዊ ድል አልተቀዳጁም ነበር:: ስለሆነም ፀረ ሕዝብ ክፍል የመንግሥቱን መኪና በቁጥጥሩ ስር ከማቆየቱም ሌላ በደርጉም ውስጥ ቢሆን ሰዎቹን ስላስቀመጠ፣ በዛን ጊዜም ቢሆን የትግል አርማው አድርጉ የወሰደው፣ ከወታደሩ ክፍል ንዑስ ከበርቴ ጋር ስልጣኑን መካፈልና "ነገር ሳይበላሽ" አመቺ ሁኔታ ጠብቆ ሥልጣኑን ባጠቃላይ በቁጥጥሩ ስር ማድረግ እንደነበር ግልጽ ነው::



ስለሆነም እነ አማን ህዳር 14 ተረሽነው በታህሣስ 11 ህብረተሰባዊነት ሲታወጅ፣ ከዚያም በመከተል የንዑስ ከበርቴውን የመደብ ጥቅም የሚያንፀባርቁ "ዲሞክራቲክ የሆኑ" ለውጦች /ለምሳሌ በሃይማኖት ማህል ልዩነት እንዳይደረግ፣ ከዚያም ኦሮምኛ በሬዲዮ እንዲተላለፍ ወዘተ.../ ሲካሄዱ፣ በፀረ ሕዝቡ ክፍል በኩል በተለይ በነቃው አድሃሪ ዘንድ እነዚህን ለውጦች ቀስ በቀስ ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝና በነዚሁ ለውጦች ላይ ለመደላደል ተስፋ ተጥሎ ነበር:: በኢትዮጵያም ተራማጆችና በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ይህ "ሕብረተሰባዊነት" የለውጥ ጭላንጭል ሆኖ ቢታያቸውም በመሠረቱ ያተኩሩት ስር ነቀል ለውጦች ላይ ነበርና፣ በተለይ የመሬትን ጥያቄ አንግበው ይዘው ቆዩ::

ከዚህ ለውጥ በኋላ የተደረገው ከፍተኛ ትግል፣ ተራማጅ ግለሰቦችም የደርጉን ሰዎች ለመገፋፋት ባደረጉት ጥረት የካቲት 25 ያ የምናውቀው የመሬት አዋጅ ታወጀ:: በዚያም እለት ፀረ ሕዝቦች "ነገር ሳይበላሽ" አዝማሚያውን እንቀለበስ ብለው እንደተነሱ ሁሉ፣ በዚች እለት "ነገር መበላሸቱ" በትክክል ታይቷቸዋል፣ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም ታይቶ የማይታወቅ በሰላማዊ ሰልፍ ደስታውን ገለጠ:: እናም በውጭ የምንገኘው ከፍተኛ ደስታ ተሰማን፣ ከማህላችንም "ፋሽስቶች" መንግሥት በ"ሕዝባዊ"መንግሥት ሊተኩ የተነሱት ግራ ተጋብተው የኢትዮጵያ ገበሬ መሬት አገኘ አላገኘ ደንታ የላቸውምና "ሙሶሊኒም የመሬት አዋጅ" አውጇ ነበር በሚል አስቂኝ ምክንያት ግራ አለመጋባታቸውን ሊያሳዩን ሞከሩ:: በሲ አይ ኤ የተመለመሉት መሪዎቻቸው አዋጁን እንዲቃወሙ ገፋፋቸውና በየጉባኤው አዋጁን አወገዙና ተለያየን::

የሆነው ሆኖ ይህ ስር ነቀል የመሬት አዋጅ በእውነቱ ለመላው የኢትዮጵያ ተራማጅ ከፍተኛ የትግል ምዕራፍ ከፍቶለታል:: ለብዙ ዓመታት "የኢትዮጵያ ገበሬ የኢትዮጵያ አብዮት ተሸካሚ ነው" ስንል የቆየነው፣ ስለዚም "መሬት ላራሹ" ይሁን ብለን የታገልነው፣ ከእንግዲህ አባባላችንን በተግባር ወደመተርጎም እንደተሸጋገርን ተረዳን::

የመሬት አዋጁ ከታወጀ በኋላ አዋጁን በሥራ ለመተርጎም በተደረገው ትግል የኢትዮጵያ ተማሪዎች በእድገት በህብረት የሥራ ዘመቻ አማካይነት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: ተራማጅ ቡድኖችም በዚሁ አኳያ ከፍተኛ ትግል አድርገዋል:: ከዛን ጊዜም ጀምሮ በገጠሩ ባላባትና በገበሬው ማህል ያለው የመደብ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተፋፋመ ሲሄድ፣ የገጠሩ ባላባት በመንግሥቱ ቢሮክራሲ ላይ ተስፋውን ጥሎ ወደ ተቃዋሚነት ተሸጋገረ:: በየገጠሩ የባላባት ሽፍታ ቡድኖች ተቋቋሙ:: ባላባቶች ደርግን "አይገነን ሳፈር" ብለው ተነሱ::

ይህ ሁሉ ግፍም አዝማምያ ለተራማጆች ቢከፈትላቸው ያንኑ ያህል ደግሞ ፀረ ሕዝቦች ሰሙት ከእንግዲህ ትግሉ በይበልጥ የከረረ እንደሚሆን ግልጽ ነበር:: የተባለውም አልቀረም፣ በተለይ የትግል ዘዴ ይሁን እንጂ በየፊናው በፀረ ሕዝቦችና በሕዝቡ ማህል ይህ ነው የማይባል ፍልሚያ ከመቼውም ይበልጥ ቀጥሏል::

እንግዲህ የመሬት አዋጁ መታወጁ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ካለን አይቀር ዘዚ አዋጁ ድምር በፀረ ሕዝቡ ክፍል የታዩትን የትግል ዘዴዎችና የትግል ፍሬ፣ እንዲሁም በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የተካሄደውን ትግልና የሰጠውን ፍሬ ወደ መመርመሩ እንለፍ:: በነገራችን ላይ ከአማን አንዶም ከስልጣን መውረድ እስከ አስቸኳይ ጊ.አዋጁ ብለን የሰየምነውን ክፍል አይነተኛ የሚያደርገው ይህ ነጥብ ነው::

<u>ሀ/ የፀረ ሕዝቦች ትግልና የትግል ውጤት</u>

ይህን ጥያቄ በዝርዝር ከመመለሳችን በፊት ፀረ ሕዝብ ብለን የሰየምነውን ክፍል ዝርዝር ይዘት ለመተንተን እንሞክር::.

ባገራችን በኩል ካንዱም ሁለቱ የጠቆምናቸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዘመናት ጠላቶች አሉ:: እነሱም ኢምፔሪያሊዝም የባላባቱ መደብና የቢሮክራቱ ከበርቴው ናቸው:: በሌላ በኩል ግን ለፀረ ሕዝቡ ክፍል አዲስ ገቢ የሆነለት የንዑስ ከበርቴው የቀኝ ክንፍ ከዛን ጊዜ ጀምሮ /በተለይ ከመሬት አዋጁ ወዲህ/ ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ሚና መጫወት ጀምሯል:: የንዑስ ከበርቴውን የቀኝ ክንፍ በሚመለከተው በኩል ከፍ ብለን እንዳልነው የየካቲት እንቅስቃሴ እንደ ማንናውም ታሪካዊ እንቅስቃሴ በተራማጆች ዘንድ ከፍተኛ ክርክር፣ ከዚም አልፎ የመስመር ትግል ማስከተሉ አልቀረም ነበርና ይህ የመስመር ትግል የንዑስ ከበርቴው የቀኝ ክንፍ አብዮቱን የሚክዳበትን አዝማምያ ከፍቷል:: በነዚህም ክርክሮች የታዩት ሁለት መስመሮች /ዛሬ የት እንደደረሱ እናውቃለን/ በዛን ጊዜ ስለ ጊዜአዊ ተጨባጭ ሁኔታና ስለ መጪው የትግል አቅጣጫ በጓደኞች ማህል የሚደረጉ ክርክር ነበሩ:: ደርጉ "ፋሽስት" ነው ሲሉን አይደለም "በደርጉና በሕዝብ ጠላቶች ማህል ቅራኔ አለና በቅራኔው እንጠቀም" ስንላቸው "ደርጉ የፋሽስት ምርጥ መኮንኖች ቡድን ሲሉን" በደርጉ ውስጥ ግራና ቀኝ ክንፍ አለ" ስንላቸው፣ ከዚም "ካሁኑ ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ሲሉ "የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ረጅም ትግል እንጂ መንግሥት በመመራረጥ አይመጣም" ስንላቸው፣ በመጨረሻ የኢትዮጵያ ሁኔታ እንደሚያጋልጥልን በሚገባ እናውቅ ነበር:: ስለ ሆነም ትግሉ በተራመደ ቁጥር በሳይንሳዊ ትንተና ወደፊት በገፋሙ፣ እነሱ በበኩላቸው ከስህተት ወደ ስህተት ከዚም ወደ ጥፋት ሲሸጋገሩ አንድ ዓመት አብረን ታገልን:: ከፍ ብለን እንዳልነው "ፋሺስት" ብለው ነበርና" የመሬቱን አዋጁ "መቃወም ግድ ሆነባቸው:: ይህ በሆነበትም ጊዜ የመሬትን ጥያቄ በመሰለ ወሳኝ ጥያቄ ላይ ለንታረቅ ባለመቻላችን ተለያየን::



እነሱም እንዳልነው ሁሉ ለፀረ ሕዝቡ ቡድን አዲስ ገቢ ለመሆን በቁ:: ከመሬቱ አዋጁ በኋላ በተደረጉት ትግሎች ሁሉ ፀረ ሕዝብነታቸውን በገቢር እያስመሰከሩ ይኸው ዛሬ የደረሱበት ደርሰዋል:: ግን እንግዲህ ያቀራረጠን ያ የመሬት አዋጁ መሆኑን መገንዘብ አለብን:: ከዚም የፀረ ሕዝቦችን የትግል ዘዴ ስንመረምር፣ የነሱንም ቦታ በትክክል መጠቆም አለብን ማለት ነው:: ለማንናውም ወደ ምርመራችን እንሸጋገር::

የመሬት አዋጁ ከመታወጁ በፊት የአድሃሪያች ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከሞላ ጎደል እንዳልተነካ፣ ሆኖም ግን ከፍተኛ የፖለቲካ ጥቃት ደርሶባቸው እንደ ነበር አይተናል፣ ስለሆነም እንዲ በእንዳልካቸው ከዚም በአማን አንዶም ጋር የ60 ሰዎች መገደል ወዲያውኑ በሰበት ወራ የመሬት አዋጁ መታወጁ በአድሃሪያች ዘንድ ከፍተኛ ሽብር በመፍጠሩ ከዛን ጊዜ ወዲህ በትግል ዘዴያቸውም ሆነ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ቦታ ተቀይሯል:: ስለዚህ የያንዳንዳቸውን ሚና ለየብቻ ለማየት እንሞክር::

የባላባቱ መደብ በኤኮኖሚ ደረጃ ለመጀመሪያ የተመታው በመሬት አዋጁ ነበር:: ይህ አዋጁ በወጣበት ጊዜ በገጠር የተገኘው ባላባት እንዲሁም በተከማ ከነበረት ማህል ከእስር የተረፈው የከፍተኛ ባላባት ሰፈር እንደውነቱ ከሆነ በመጀመሪያ በአዋጁም አላመነበትም ነበር:: ቢያንስ አዋጁ በሥራ ላይ አይውልም በማለት ተስፋ አድርጎ ነበር:: ይሁንና በዘማቾች አነቃቂነትና አደራጅነት ይህ አዋጁ በሥራ መተርጎም በጀመረበት ጊዜ መሬታቸውን ትተው ጫካ የገቡት ወይም ደግሞ ወደ ከተማ የፈለሱት ባለመሬቶች ቁጥር ከፍተኛ ነበር:: ይህም በሆነበት ጊዜ ከፍተኛ ባለመሬቶች ቢያንስ በገጠር በቁጥጥራቸው ሥር የነበረውን አስተዳደር በከፊል አጥተዋል:: ስለሆነም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የባላባቱ መደብ ባጠቃላይ ሲታይ የመንግሥቱ ተቃዋሚ በመሆን በየመንደሩም ቢሆን የታጠቀ "ሬዚስታንስ" አሳይቷል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን ብዙ ባላባቶች ከነበረው ቢሮክራሲ ጋር በመተባበር ከደርጉ ውስጥም በነበሩት ሰዎች በመረዳት ለፀረ አብዮት ግባቸው በራሱ በመንግሥቱ ይጠቀሙ እንደነበር የማይታበል ሃቅ ነው:: የ"ኢትዮጵያ ሶሻሊዝም" አፍቃሪ ነገር ግን የመሬቱ አዋጁ ተቃዋሚ የነበረው ሲሳይ ሃብቱ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው:: የገጠር አጥቢያ ዳኛዎች ፖሊሱ ወዘተ... የመሬት አዋጁን በሥራ ላይ መዋል በመቃወም፣ ከዚም አልፈው የአብዮታውያን ዘማቾችን ትግል በማደናቀፍ ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል::

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ቢሮክራሲው በገጠር ከባላባቱ ከመተባበሩም በላይ በከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ፣ ከደርጉ ጋር በግልጽ ቅራኔ ውስጥ የገባው ከዚሁ ከመሬት አዋጁ በኋላ ነው::

ለምን ቢባል መልሱ ቀላል ነው:: የኢትዮጵያ ቢሮክራሲ ያካሄዱ የነበረት ቀንደኛ መሪያቸ በዙዎቹ ባለመሬት ነበሩ:: ቢያንስ በዘውድ አገዛዙ ከታላላቅ ባለመሬቶች ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ከዚያ አልፎ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ 90% የሆነው ገበሬ በጭቆና መላቀቅ የራሳቸውን የመደብ ህልውና ከጥያቄ ውስጥ እንደሚያስገባው በሚገባ ተረድተውታል:: ሆኖም ግን እነሱም ቢሆኑ በመንግሥት መሣሪያ ላይ / በቶት አጀራተስ / ከፍተኛ ቁጥጥር ስለነበረባቸው፤ በደርጉም ውስጥ ተወካይ ስለነበራቸው፤ ለፀረ አብዮት ግባቸው በመንግሥቱ ተጠቅመዋል:: ግን እንግዲህ በተለይ እነሱን የጎዳቸው /ከመሬት አዋጁ እኩል/ በሐምሌ 19 የታወጀው የከተማን ቦታና ትርፍ ቤትን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያደረገው አዋጅ ነው:: በከተማ በሚያከራዩት ቤት የነበራቸው ገቢ፤ ይህንንም ገቢያቸውን የሚያውሉበት የፀረ አብዮትና የፀረ ሕዝብ የትግል ሚናቸው በድንገት ድርቀት የገጠመው ከዚህ አዋጅ በኋላ ነው:: ስለዚህም ይህ አዋጅ ባጠቃላይ ለነ አድሃሪያቸ በተለይ ለከተማው ቢሮክራሲ ሁለተኛ የኢኮኖሚ ጥፊ ነበር:: በነገራችን ላይ ይህ ሃቅ ሆኖ ሳለ የንዑስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ " የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች የተወረሱት በቀበሌ ማህበራት አማካይነት የከተማውን ነዋሪ ለመስለል ነው" ሲሉን፤ በእውነቱ እነዚህ ሰዎች ለማ እንደቆሙ ለመገመት አያዳግትም:: እነዚህ አርምጃዎች ታላላቅ ነጋዴዎቻችንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለነኳቸው ይህ ክፍል ከዛን ጊዜ ጀምሮ በግልጽ የኢኮኖሚ አሻጥሮችና በጥቁር ገበያ ተሰማርተዋል:: ከኢምፔሪያሊስቶች ጋርም የነበረውን ጥብቅ ግንኙነት ደርጉን ለመጣል ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የተጠቀመው ከዚህ ወቅት በኋላ ነው::

መቼም ኢምፔሪያሊስቶች የኢትዮጵያን ሕዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከመጀመሪያው ጀምሮ በቀስታም ሆነ በመንግሥት ግልበጣ ለመቀልበስ ለደቂቃም አላረፉ:: ከዚህን ጊዜ እንስቶ እስከዚህ ጊዜ እንቅስቃሴውን ተተውት ነበር፤ ከዚያም ሊቀለብሱት ሞከሩ ለማለት አይቻልም:: ሆኖም ግን ለመቀልበስ የተጠቀሙበትን ታክቲክ እንደወቅቱ መጠቆም ይቻላል:: መጠቆም ይጠቅማል:: ደጋግመን እንደተናገርነው ዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካን፤ እንዳልካቸው እንዲሳካለት አጥብቆ ሙግተዋል:: ከዚያም የብዙ ዘመን ወዳጃቸው ሃይለ ሥላሴ ሲነሳ፤ አማን አንዶም እስካለ ገዱ የለም የሚል ግምት ነበራቸው:: ስለሆነም እስከዚ ጊዜ ድረስ፤ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን በለጋነቱ ለመቀንጠስ ይፈልጉ እንጂ ደግ በተባለው ውስጥ የ"መሸጉትን" ጠላቶቻቸውን ለመደምሰስ ይቃጡ እንጂ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መሠረታዊ ስምምነት ነበራቸው ለማለት ይቻላል::



ሆኖም ግን አማን አንዶምና 60 ሰዎች ሲገደሉ በግልጽ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ቅራኔ በመግባት፤ መሣሪያ አንስጥም ማለት ጀመሩ፤ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ እንደ ዘንበ ሲረግፍ ያላለቀሱት በ60ዎቹ ሰዎች መሞት የኢትዮጵያን አብዮት አበተዓደር አረመኔነት ሊያሳዩን ሞከሩ:: ከዚያም የመሬት አዋጁ ከታወጀ በኋላ የሸፈቱትን ባላባቶች በገንዘብና በሞራል መርዳት በግልጽ ጀምረዋል:: አሰከሁንም እየረዱ ናቸው:: ይሁንናም ኢምፔሪያሊስቶች እንዲህ በቀላሉ የማይሸበሩ መሆናቸውን በዛን ወቅት በሚገባ አሳይተዋል:: በነበረው አዘማምያ፤ በተለይ ደርግ " ሕብረተሰባዊነትን" አውጆ የሶሻሊስት አገሮች አቀፈውን ደግፈውን ይዘዋል ብሎ ተበፋ በጣለበት ዘመን፤ ከኢትዮጵያ ጋር የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ መግባት እንደማያዋጣቸው/በሚገባ ተረድተዋል:: በነገራችን ላይ እንኳን ኢትዮጵያ ቀርታ 30 ዓመት ሙሉ በቦንብ የደበደቧትን ደቡብ ቬትናም አሁንም ግንኙነት እንመስርት ይልዋታል:: ስለሆነም ለነሱ በዛን ጊዜ ያዋጣ መስሎ የታያቸው የትግል ዘዴ፤ ባንድ በኩል ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ግንኙነት በመቀጠል በተለይ ለሶቭየት ህብረት መንገዱ መዝጋት፤ በሌላ በሌላ በኩል ከደርጉ ውስጥና ከደርጉ ውጭ ያሉትን ሃይሎቻቸውን አስተባብሮ የደርጉን ግራና ተራማጆችን መደምሰስ ከዚያም የአብዮቱን አቅጣጫ መቀየር ነበር:: ደግሞ ነገሩን ጠጋ ብለን ካየነው፤ አሜሪካኖች ሃይለ ስላሴ ቢሄዱ እንዳልካቸው፤ እንዳልካቸው ቢሄዱ አማን እንዳሉት፤ ሁሉ አማን ቢሄዱ ቢሳይ ማለታቸው አልቀረም::

በዚህ ከፍ ብለን በዘረዘርነው የፀረ ሕዝብ ኃይሎች ተርምስ ውስጥ፤ ወደደም ጠላም ከፍተኛ ቦታ መያዝ የጀመረው የንዑስ ከበርቴ ክፍል በገቢር የማይናቁ ፀረ ሕዝብ ድርጊቶች ፈጽሟል:: እንደውነቱ ከሆነ ይህን በምንል በት ጊዜ ነገሩን ጠጋ ብሎ ላላየው ወይም ደግሞ በተባለው ቡድን ውስጥ እየተሳተፈ የኢትዮጵያን ሕዝብ የጠቀመ የመሰለው ሃቀኛ ተራማጅ፤ በሃቅ ላይ ያልተመረከዘ አስተያየት ይመስለው ይሆናል:: ሆኖም ግን ማንኛውም አብዮታዊ አንድን ድርጊት የሚያየው ከድርጊቱ ተጨባጭ ውጤት እንጂ አድራጊው ከሚያስማው ምኞት ስላልሆነ፤ የንዑስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ ሚና በድፍረትና በሃቀኝነት ለንመረምረው ይገባል:: አሁን ለምባሉ ደርግ ሕዝባዊ መንግሥት አይደለም:: ስለዚህም ይህን ደርግ በደፈናው መቃወም፤ እነሱ እንደሚሉት" ከመቃወም ይልቅ ማውገዝ" ከተቻለም አስከነአካቴው " ፋሺስት" ማለት በጣም ተራማጅነት <u>ለመሰለ</u> ይቻላል:: ግን ደግሞ ከዚህ በመነሳት በሕዝብ ትግል የተገኘን የመሬት አዋጅ " ፋሺስት" አውጇታል ብሎ መቃወም፤ በገቢር ከጠላት ጋር መሰለፍ ነው:: ይህ ደግሞ ሁለት ነገሮች ያስከትላል:: ባንድ በኩል ተራማጅነት መስሏቸው በዚህ አቋም ስር የተሰለፉት ሃቀኛ ታጋዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁኔታውን እየተረዱ አቋሙን ትተው ይሄዳሉ፤ በሌላ በኩል በመጀመሪያ በተራማጅ ቃላቶች የተደናገጡት አድሃሪያች ከጊዜ ወደ ጊዜ ይህ አቋም የሚያመጣላቸውን ጥቅም በመረዳት አቋሙን እያቀፉና እየተከራከሩለት ይመጣሉ::

ኢህአፖን የገጠመው "አደል" ይበው ነው:: በሌላ አነጋገር ኢህአፖ ዛሬ የሆነውን ሊሆን የቻለው በቃላት ተራማጅ በድርጊት ፀረ ሕዝብ በመሆኑ ብቻ ነው:: በቃላት ተራማጅነቱን እሱ ራሱ ሲበዛ አሳይቶናልና አንመለስበትም:: ዋና ፋንታ በደርጊት ፀረ ሕዝብነቱን ማሳየቱ ነውና አንዳንድ ምሳሌ ጠቅሰን እናለፋለን:: ይሁንና በዚህም በኩል ብዙ ፅሑፎች ወተዋል:: ከተፈለገ በዚሁ አርእስት ብቻ መጽሐፍት መጻፍ በተቻለ ነበር:: ነገር ግን ከዋናው አርእስታችን ላለመውጣት ያህል፣ ከፍ ብለን በጠቀስነው ወቅት ውስጥ ማለትም ከመሬት አዋጅ በኋላ ባሉት ወቅት ውስጥ ከሃዲው ቡድን የፈጸማቸውን ፀረ ሕዝብ ድርጊቶች ጠቅመን እናለፋለን:: በዚህም በተባለው ወቅት ውስጥ ለፀረ ሕዝቡ ሰፈር የሰጠውን አገልግሎት ለማሳየት እንሞክራለን::

እንግዲህ ይህን ነጥብ በምንተነትንበት ጊዜ የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች መመለስ አለብን:: በዛን ጊዜ የከሃዲው ቡድን ፊታውራሪ የነበረውን ኢህአፖን የሚከተሉት እነማን ነበሩ፤ እንዲትስ ለፀረ ሕዝብ ድርጊቶች ሊያሰልፋቸው ቻለ በነበረው የሁለት መስመር ትግል የአብዮታዊውን መስመር ጥልቀት ያልተረዱ፣ "ሕዝባዊ" ካልሆነ ደርግን ከመሰለ መንግሥት የሚመጣ አዋጅ መደገፍ እውነትም አድሃሪነት የመሰላቸው ብዙ የተወናበዱ ወጣቶች "ቶሎ ሲቪል ይውደም" "ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ይቋቋም በሚለው ጭፍጭ መፈከር ስር ተሰልፈው ነበር:: ከነዚህም ውስጥ ወደዶም ጠሎም የዘመቱ ነበሩ:: ኢህአፖ የተጠቀመው በነዚህ በቅን ወጣቶች ነው:: ያገለገለው ግን በአመራሩ የተሰገሰጉትን የፀረ ሕዝቦች ጥቅም ነው:: የመሬቱ አዋጅ ሲታወጅ፣ ቢያንስ ባንድ ለቀ እትም ላይ "ኮከራሲያ" አዋጁን አድንቆ ፋሺስት የሚሏቸውን ደርጎች ከሰፊው ሕዝብ አብራክ የወጡ "ብሏቸው ነበር:: ነገር ግን ይህ አቋም በዛም አልቆየ ወዲያውኑ በዚሁ በኢህአፖ መሪነት የመሬት አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገውን ትግል ለማደናቀፍ ብዙ አሻጥሮች ተፈጽመዋል:: በገጠር የሰተማሩት ተማሪዎች ገበሬውን እንዳያደራጁ ከቻሉም እንዳይዘምቱ ለማድረግ ብዙ ጥረት ተደርጎዋል:: ለዚህም የሚሰጡት ምክንያቶች ደርጉ ባላባቶችን ይረዳል ስለዚህ ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት ካልተቋቋመ አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል መታገል፣ ገበሬውን ለደርጉ ማሰለፍ ነው የሚሉ ሰበቦች ነበሩ:: ከዛም አልፎ ገበሬውን በደርጉ ላይ ለማስነሳት፣ ከተማውን ለማስደንገጥና ሽብር ለመፍጠር "ዛም ሁኔታው አመቺ ቢሆን " ሕዝቡ ስልጣን እንዲይዝ" እየተባለ ከፍተኛ ፀረ ሕዝብ ድርጊቶች ተፈጽመዋል:: ለምሳሌ በመቂ አካባቢ በኢህአፖ ጭፍሮች አማካይነት የተከናወነው ፀረ አብዮት ድርጊት እንጥቀስ :: የመሬቱ አዋጅ ከታወጀ በኋላ በኢህአፖ የተመረዙ ዘማቾች በመቂ አካባቢ ገበሬውን ይሰበስቡና በሰላማዊ ሰልፍ አድርገን መቂ ሄደን የተወሰኑ ጥያቄዎች ለመንግሥት እናቅርብ ይሉታል:: ገበሬው ይስማማና፣ ተሰልፎ ወደ መቂ ያዘግማል::



በዚሁ ጊዜ መቂ የቀዩ የኢህአፖ ደጋፊዎች " ገበሬው ከተማውን ሊዘርፍ ዘምተዋል" የሚል ማስጠንቀቂያ ለከተማው ያስወራሉ:: ከተማው በሩን ዘግቶ መሳሪያውን መዞ ሲጠብቅ ያከባቢው ገበሬዎች መቂ ከተማ ሲደርሱ ያያል:: በዛን ጊዜ ከተማው ተደናግጦ ተኩስ ይከፍትና ገበሬዎች ሲያቀብል፣ ገበሬዎች አፀፋውን ይመልሳሉ፣ ብዙ ንፁህ ደም ይፈሳል::

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚደረገው በ" ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ስም ነው ::የኢህአፖ ፀረ ሕዝብ ድርጊት በዚህ አይወሰንም:: በገበሬው ዘንድ "እተረበ ተራኩቱር ጠይቁ" የመሳሰሉ ቅስቀሳዎች ለመደረጋቸው ማህበ ማህበራቸን ብዙ ሃተታ አንመለስበትም::

ለማጠቃለል ያህል ይህ ቡድን ከመሬቱ አዋጅ ወዲህ በተራማጅ ስም የፈጸማቸውን ፀረ ሕዝብ ድርጊቶች መረዳት፣ በገጠር ብቻ ሳይሆን በከተማም ያከናወናቸውን አሻጥሮች መገንዘብና ማጋለጥ አለብን እንላለን::

ለ/ የሕዝቡ ትግልና የትግል ውጤት

በተባለው ወቅት ውስጥ /ለማስታወስ ያህል ከነአማን ከሰልጣን መወገድና በተለይ ከመሬት አዋጅ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድረስ/ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አይነተኛ ትግል አካሂደዋል:: ብዙ መሠረታዊ ድሎችንም ተቀዳጅተዋል::

አቀማችን በፈቀደልን ኖሮ በየቦታው የተካሄዱትን ትግሎች፣ ሰፊው ሕዝብ የገጠሙትን ችግሮችና ያገኙትን የትግል ፍሬዎች በዘረዘርን ነበር:: ይሁንናም ዋና ዋና ነጥቦቹን ለማስቀመጥ እንሞክራለን:: ለዚህም አሰማችን 1ና የመሬቱን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የተደረገውን ትግል፣2ና የተገኙትን ለቀ ለቀ ድሎችና የተደረጉትን ትግሎች ለመተንተን እንሞክራለን::

ከፍ ብለን እንዳስቀመጥነው ይህን ወቅት አይነተኛ ያደረገው፣ የመሬት አዋጅ መታወጅና ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የተደረገው ትግል የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል አዲስ ምዕራፍ ውስጥ ማስገባቱ ነው::

በየካቲት 25/1966 ይህ አዋጅ ሲታወጅ በብዙ ሰፍራዎች እርሻ ተጀምሮ ነበር:: በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይ የተጀመረው እርሻ መሬቱ በታላላቆ ባለመሬቶች እጅ እያለ ነበር ማለት ነው:: በብዙ ሰፍራዎች የኢትዮጵያ ገበሬዎች ይህን የጭቆና ስርዓት ለመቋቋም ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጉ እንጂ ኃይላቸውን የሚያስተባብር፣ከጎናቸው ቆሞ ትግላቸውን የሚያቀነባብር ድርጅት አልነበረም::

አዋጁ በታወጀበት ጊዜ፣ ከጐ ቸው የተሰለፉ ተራማጆች እሉ ቢባል፣ የእድ
ገት በህብረት ዘማቾቹና፣ አንዳንዱ በየገጠሩ መሥሪያ ቤት የሚገኙ ተራማጅ
ግለሰቦች ብቻ ነበሩ ለማለት ይቻላል:: በሌላ በኩል ግን፣ ባላባቱ በመሳ
ሪያም ሆነ በአስተዳደር በኩል የማይናቅ ኃይል ነበረው:: በየገጠሩ የተን
ሰራፋው ቢሮክራሲ ከባላባቱ በጥቅምም ሆነ በዝምድና የተባበረ፣ ገበሬውን
ለመበዝበዝ የተቋቋመ መሣሪያ ነበር::

እንግዲህ አዋጁ በታወጀበት ጊዜ የነበረው የኃይል አሰላለፍ ይህ
ነበር:: ስለሆነም የባላባቱን ስርዓት ሥረ መሠረት የሚነካ አዋጅ በታወጀ
በት ጊዜ ባላባቱና የገጠሩ ቢሮክራሲ ምን ያህል እንደተደናገጡ ለመገመት
ይቻላል:: ሆኖም ግን፣ ከመደናገጥ አልፈው አዋጁን ለመታገል በግልጽ እንደ
ሚሰለፉ የማያጠራጥር ሃቅ ነበር::

በመጀመሪያ ደረጃ የገጠሩ ባላባት ተስፋ ጥሎ የነበረው፣ ገበሬው
ተደራጅቶ ባላባቱን ተቋቁሞ በደርጉ የመሬት አዋጅ በመጠቀምና መሬቱን
ለመደላደል ኃይል የለውም በሚል ግምት ነው ለማለት ይቻላል:: እንደውነቱ
ከሆነ አዋጁ በተሰማበት ጊዜ፣ የገጠሩ ቢሮክራሲ በተለይ የአዋጁ ይዘት
በገበሬው እንዳይታወቅ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጉም በላይ፣ የተጀመረው እርሻ
ሰብል እስኪያሰገባ ድረስ የመሬት ድልድል እንዳይደረግ ከፍተኛ ጥረት አድ
ርጉ ነበር:: ይህም የሚያሳየው በባላባቱ በኩል የደርጉን የመሬት አዋጅ
በሥራ እንዳይውል መቋቋም ይቻላል የሚል ግምት እንደነበር ነው:: ይሁንና
በተለይ በዘማቾቹ ብርታት የመሬቱ ድልድል፣ ወዲያውኑ እንዲደረግ በተደረገው
ጥረት፣ ከዛም ገበሬዎች በማህበር እንዲደራጁ በተደረገው ቅስቀሳ፣ ባላባቱ
ከነበረው ግምት ወደ ኋላ ፈቀ ማለት ተገዷል:: የተጀመረው እርሻ ሰብል
እስኪያሰገባ አዋጁ በሥራ ላይ እንዳይውል፣ በማህሉም በመንግሥት ደረጃ
አዋጁ እንዲሰረዝ፣ ተስፋ አድርጉ የነበረው ባላባትና የገጠር ቢሮክራት፣
ወደደም ጠላም መሬቱን ማስረከብ ተገዷል:: በመላ ኢትዮጵያ የገበሬ
ማህበራት ማበብ ሲጀምሩ፣ በዘማቾቹ አደራጅነት የመሬቱ ክፍፍል በሥራ ላይ
ሲውል፣ ባላባቱ ከላይ ሆኖ የአዋጁን በሥራ ላይ መዋል ከማፈን አልፎ፣
ከውጭ ሆኖ የአዋጁን በሥራ መተርጐም ወደማደናቀፉ ተሸጋገረ ለማለት
ይቻላል:: እንግዲህ መሬቱ በገበሬው እጅ ከገባ ዘንዱ ለባላባቱ የሚቀረው
የትግል መድረክ፣ ይህ መሬት መከፋፈል ውጤት እንዳይሰጥ፣ በምርት ደረጃ
ውድቀት እንዲፈጠር ባገሪትዋ ረሃብ እንዲሰፍንና ሽብር እንዲነገስ ነበር
ለማለት ይቻላል::



በዚህም እንፃር በገጠሩ ባለመሬትና በገጠሩ አስተዳደር ተበበር
ከፍተኛ ትግል ተካሄዷል:: የተጀመረው እርሻ እንዲቋረጥ፣ የታረሰው
መሬት እንዳይዘራ በሬዎቹን በርካሽ ዋጋ በመሸጥ፣ በጉተራ የነበረውን የዘር
እህል ማቃጠል ወይም መደበቅ የባለመሬቶቹ የትግል ዘዴ ሆኖ ነበር::
በዚህ ጥረት የገጠሩ አስተዳደር በሚገባ ተካፍሏል:: የባለመሬቱ ከብቶቹ
እንዳይነጠቁ፣ በጉተራው የተከመረውን እህል እንዳይነካ፣ ከየመሥሪያ ቤቱ
ትዕዛዝ እየተላለፈ፣ ገበሬዎቹን ለማስፈራራት ሞክሯል:: ይህንን ችግር
ለመቋቋም ቆርጠው በተነሱ ዘማቾች ላይ ክስ በማቅረብም ሆነ ጥቃት በማድረስ
የገጠር ቢሮክራሲ ከባላባቱ ጐን በከፍተኛ ደረጃ ተሳትፏል::

ይሁንናም፣ ይህ የአሻጥር ሙከራ ውጤት አልሰጠም:: በብዙ ቦታዎች
በውዴም ሆነ በግድ፣ አብዮታዊ ዘማቾችና ገበሬዎች፣ የእርሻ በሬዎቻቸውንም
በማስቀረት፣ በጉተራ የነበረውንም እህል በመከፋፈል፣ የባላባቱን አሻጥር
ሊቋቋሙ ችለዋል:: ስለሆነም፣ አገራችንን በረሃብ ወጥመድ ለመጣል የተነ
ሱት ባላባቶችና ቢሮክራቶች እቅዳቸው ሳይሳካ ቀርቶ፣ እንዲያውም በዚን
ዓመት ያገሪትዋ ምርት ሊጨምር ችሏል::

ሌላኛው የባለመሬቶች ተቃውሞ፣ በመሳሪያ ትግል በኩል ነበር::
መሬቱ እንደተወሰደባቸው፣ መሳሪያቸውን ይዘው በየጥሻው የገቡ የባለመሬ
ቶች ብዛት የሚናቅ አይደለም:: በተሰማሩበት የመሳሪያ ትግል በገበሬዎች
ላይ ብዙ ጥቃት አድርሰዋል:: ብዙ ከብቶች ፈጅተዋል፣ የእህል ማሳ አቃጥ
ለዋል፣ ግንባር ቀደም ዘማቾች ላይ ከፍተኛ ጥቃት አድርሰዋል:: በብዙ
ቦታዎች ለዚህ አላማቸው የገጠር ባለሥልጣኖች እርዳታ አልተነሳቸውም:: ሆኖም
ግን፣ በዚህም በኩል ቢሆን በገጠር የተቀጣጠለው አብዮታዊ ማዕበል ለገቱት
አልቻሉም:: ከፍተኛ የፖለቲካ ንቃት ባይኖረውም ከራሱ ሰቃይና መከራ ብዙ
ትምህርት የቀሰመው የኢትዮጵያ ገበሬ ከአብዮታዊ ዘማቾች ጋር በመተባበር
በቆራጥነት ሊቋቋማቸው ችለዋል:: እስከዛሬም፣ የኢትዮጵያ ገበሬ "አስታጥቁኝ"
ብሎ የተነሳው እነዚህ የታጠቁ ጠላቶቹን ከምድር ገፀ ለማጥፋት ነው::
ስለሆነም ገበሬውን ለማስታጠቅ "ችላ" ማለት፣ ፍፁም ፀረ ሕዝብነት ለመ
ሆኑ፣ ከዚህ በመነሳት ብቻ መረዳት ይቻላል::

የሆነው ሆኖ በየካቲት የተጀመረው እርሻ ቀጥሎ በመላ ኢትዮጵያ
ለመጀመሪያ ጊዜ ገበሬው ለገበሬው ያመረተው ሰብል መድረሱ አልቀረም፣
ደረሰ:: በዚህን ጊዜ አድሃሪዎች ያተኮሩት ገበሬውን እርስ በርስ ለማፋ
ጀት ነበር:: "ምርቱን ማነው የሚወስደው"፣ "ጉበዝ ገበሬ ሰነፍ
ገበሬ እንዴት እኩል ይካፈላሉ"፣ "መንግሥት ምርቱን በሙሉ መዝረፉ ነው"
ወዘተ...በማለት ከፍተኛ ቅስቀሳ በየፊናው ይደረግ ነበር::

እንደውነቱ ከሆነ፣ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የመሬቱ ድልድል የተደረገው አርሻ ከጀመረ በኋላ ስለነበር፣ ከዛም መሬቱ የተሰራው በዛውን ጊዜ በህብረት ስለነበር፣ ምርቱን የማከፋፈሉ ጥያቄ መጠነኛም ቢሆን ችግር መፍጠሩ አልቀረም:: በብዙ ስፍራዎችም ለዚህ ችግር እንደ መፍትሔ የተወሰደው፣ ምርቱን ለገበሬ ማህበራት አስረክቦ፣ ምርቱን በያጥ ለገበሬዎች ማከፋፈል ነበር:: በዚህን ጊዜ በብዙ ስፍራዎች የተወሰኑ ችግሮች ተፈጥረዋል:: ለምሳሌ በብዙ ስፍራዎች ገበሬው በእህልም በኩል ሆነ በገንዘብ ያጠራቀመው ነገር ስላልነበረ፣ ምርቱ ተሸጦ ገንዘብ እስኪገባ መጠበቅ አልቻለም:: አንዳንዱ ዐታዎች በገበሬ ማህበራት ውስጥ ሰርገው የገቡ ፀረ ሕዝቦችሽ የአካባቢውን ምርት ከሰበሰቡ በኋላ፣ ወደ ጉን እያሸሹ፣ በገበሬ ማህበራትና በሰፊው ገበሬ ማህል ከፍተኛ ጥርጣሬ ሊፈጥሬ ችለዋል:: በለሆነው በብዙ ስፍራዎች ለመጀመሪያው ዓመት በህብረት የተከሩ መሬቶች፣ ለሁለተኛው አዝመራ ለየገበሬው እንዲደለደሉ ተደርጓል:: ሆኖም ገን፣ መሬቱ ለየገበሬው ቢሰጥም፣ ለማህበሩ መተዳደሪያ የሚሆንና የገበሬዎችን አንድነት እንዲያስተባብር ተብሎ ጥቂትም ቢሆን፣ የተወሰነ መሬት በህብረት እንዲሰራ ተደርገዋል::

እንግዲህ፣ የመሬትን አዋጅ በሥራ ለመተርጎም የገጠሙት ችግሮች እነዚህ ቢሆኑ፣ በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ ባጠቃላይ ደረጃ አስደሳች ውጤት ሊያስገኝ እንደቻለ መገመት አያስቸግርም:: በሰንጠረዡ በገመለከተው የሚቀጥለውን እንገነዘባለን::

| ክፍለ ሃገር | የማህበራት ብዛት | የአባላት ብዛት |
|---|---|---|
| ሸዋ | 4.450 | 1.029.136 |
| ወለጋ | 2.007 | 372.737 |
| ኢሉባቦር | 1.008 | 176.342 |
| አረሲ | 1.104 | 256.384 |
| ሲዳሞ | 1.497 | 619.461 |
| በገምደር | 1.671 | 266.340 |
| ወሎ | 2.192 | 557.110 |
| ሐረርጌ | 1.807 | 549.495 |
| ጉጃም | 1.828 | 316.004 |
| ትግሬ | 1.289 | 380.071 |
| ገሙ ጎፋ | 281 | 96.151 |
| ባሌ | 793 | 110.792 |
| ከፋ | 1.571 | 385.161 |
| ድምር | 21.498 | 5.115.192 |

/የካቲት 25/68/ የመሬትና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር መጽሔት::



በተጨማሪ፣ ከመሬቱ አዋጅ በኋላ፣ በገጠር የተፋፋመውን የመደብ ትግል፣ በገመለከት፣ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ባንዱ በኩል ሰፊው ገበሬና ተራማጅ በሌላ በኩል ባላባቱና ቢሮክራሲው ጥረት ባለ ሁኔታ ተለይተው ከፍተኛ ፍልሚያ ላይ እንዳሉ እንረዳለን:: ይህ ደግሞ፣ ገና ለወደፊት ለሚቀረው ትግል፣ ምን ያህል ከፍተኛ አስተጽዎ እንደሚሆን መገመት አያስቸግርም:: በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ ገበሬ ለፀረ ባላባታዊ ትግል በሚያደግም ሁኔታ ተሰልፍዋል ማለት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝቦችም የነፃነት ትግል ዋናውን አጋር ለትግል ማስለፋ ከፍተኛ ድል ነው:: ከዚህም አልፎ ዛሬ በገጠር ያለው ሁኔታ፣ ለወደፊቱ ሕዝባዊ አስተዳደር የጣለውን መሠረት መጠቆሙ ጠቃሚ ነው:: የተቋቋሙት የገበሬ ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች፣ የጥበቃ ጓዶች ወዘተ... ለዚህ የማያወላውሉ ተጨባጭ ምስክሮች ናቸው:: ወደዱንም ጠሉንም፣ ባላባቶችና፣ የመሬቱ አዋጅ ፋከዝምን ያስፋፋል ያሉት፣ ደስ አላቸውም አላላቸው፣ ይህ በገጠር የተጣለው መሠረት ለሕዝባዊት ኢትዮጵያ መቋቋሚያ በትር እንደሚሆን አያጠራጥርም::

ከፍ ብለን የተመለከትነው ትግል፣ በገጠር በሚካሄድበት ወቅት፣ በመላ ኢትዮጵያ በልዩልዩ ወሳኝ ጥያቄዎች አካባቢ ከፍተኛ ትግል ተካሂዷል:: ከፍ ብለን የዘረዘርነውን የልዩ ልዩ ፀረ ሕዝብ ክፍሎች የቀስቀሳ ሙከራዎች ለመቋቋምም ሆነ፣ በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ ቦታ በያዙ ጥያቄዎች ላይ ተራማጆችና ተራማጅ ድርጅቶች ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል:: በተወሰኑ ነጥቦችም ላይ አብዮታውያን ድል ተቀዳጅተዋል::

በዚህ ወቅት ውስጥ፣ በተለይ በገጠር የተፋፋመውን አብዮታዊ ማዕበል ለማፈንና ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት ቀለበስ በመገርሰስ ላይ ያለውን ስርዓት በአዲስ መንፈስ ለማደስ፣ ልዩ ልዩ ፀረ ሕዝብ ክፍሎች የተጠቀሙበትን ዘዴ ከፍ ብለን አይተናል:: በተለይ በዚህ ወቅት ከፍተኛ ትግል የተካሄደው፣ ባጠቃላይ ደረጃ ለዴሞክራሲ የተደረገው ቢሆን፣ በተለይ የኤርትራ ጥያቄና የዴሞክራቲክ መብቶች ጥያቄ ዋና ቦታ ይዘው ነበር:: ለማስታወስ ያህል፣ ከነአማን አንዶም መገደልና በተለይ ከመሬት አዋጅ በኋላ አምፔሪያሊስቶች ቢሮክራቲክ ከበርቴው እንዲሁም ባላባቱ የደርጉን ግራ ክንፍ ለመደምሰስ በሁለት ዘዴዎች እንደሚጠቀም አይተናል:: ወይንም ደርጉን እንዳለ ገለበጦ አዲስ መንግሥት ማቋቋም ለዚህም ባገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ በመፍጠር ሁኔታውን ማመቻቸት:: ወይም ደግሞ የደርጉን ቀኝ ክንፍ ማጠናከር፣ ማለትም በደርጉና በሕዝቡ መኻል ያለውን ቅራኔ ማባባስና የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል አከፋፍሎ ማዳከም::

በኤርትራ ጉዳይ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች የተከተሉት ፖለቲካ ከዚህ መድረክ አይወጣም::

ባንድ በኩል የኤርትራ ግንባር የቀኝ ክንፍ፤ በኢትዮጵያ የተቀጣጠለው የአብዮት መንፈስ የኤርትራን ሕዝቦች በራሱ ላይ እንዳስነሳበት ከዛም በኢትዮጵያ በነበረው ያልተደላደለ ሁኔታ በመጠቀም፤ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል አመቺ ሆኖ ታይቶት ነበር:: ለዚህም በየካቲት 67 አካባቢ በግንባሮቹ በኩል ከፍተኛ መነሳሳት ታይተዋል::

በሌላ በኩል የደርጉ ቀኝ ክንፍና በኢትዮጵያ የሚገኙት ፀረ ሕዝብ ኃይሎች የአብዮቱን ሂደት ለመግታትና የኤርትራንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ለማፍረስ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በኤርትራ ጦርነት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ከዛም በጦርነቱ የተነሳ አገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እንድትገባ፤ የበዢ ትምክተኝነትን በመቀስቀስ በኤርትራ ሕዝቦች ላይ አፀያፊ ጦርነት አውጀው፤ ብዙ ሕዝብ አስጨርሰዋል:: የኢትዮጵያ ተራማጆችና ተራማጅ ድርጅቶች ይህን ሴራ ለመቋቋም ቁጥር ስፍር የሌለው የሰላም ጥሪ አድርገዋል:: የኤርትራ ችግር ሊፈታ የሚችለው በሰላም ውይይት መሆኑን በመጠቆም ትምክህተኝነትንና ጠባብ ብሄረተኝነትን በመታገል ሰፊ ቅስቀሳ አድርገዋል:: ይህም ትግላቸው፤ ወደያውኑ ውጤት አያባይ እንጂ በግንቦት 68 ለታወጀው የዘጠኝ ነጥብ የፖለቲካ ውሳኔ የማይናቅ አስተዋጽዎ አድርገዋል:: በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ተራማጆች ለዲሞክራቲክ መብት ያደረጉት ተጋድሎ በተለይ የደርጉን አንድ ብሔራዊ ፖርቲ የማቋቋም እቅድ ለማክሸፍ ያካሄዱት ቅስቀሳ ከፍተኛ ቦታ ይዞ ነበር:: እንዲውም በዚህ በኩል የተደረገው ትግል ለመሬት አዋጁ ከተደረገው ትግል ቀጥሎ ይህንን የትግል ወቅት አይነተኛ ያደረገ ትግል ነው ለማለት ይቻላል:: ይቋቋም የነበረው አንድ ብሔራዊ ፖርቲ እንዴት ፀረ ሕዝብ እንደ ነበር እንዴት የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ሊገታ እንደሚችልና ያለውን ቢሮክራሲ የሚያጠነክር እንጂ፤ በቢሮክራሲውና በባላባቱ ስርዓት መቃብር ላይ ለሚያብበው ሕብረተሰባዊ ስርዓት ፀር እንደሆነ በሚገባ አሳይተዋል::

ያደረጉትም ከፍተኛ ትግል፤ የተባለውን ፖርቲ መቋቋም በሚገባ ሊገታ በመቻሉ የወቅቱ ታላቅ ድል ነበር ለማለት ይቻላል:: በዚህ ወቅት ውስጥ ሌሎች መሠረታዊ ድሎች ተገኝተዋል:: ከነዚህም አንዱ ሐምሌ 19–67 የታወጀው የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያደረገው አዋጅ ነው:: የዚህን አዋጅ ተራማጅነት ለመረዳት፤ ሁለት ነጥቦች ማንሳቱ ይጠቅማል::



1ኛ/ ከገጠር የፈለሱ ባለመሬቶች በከተማ መሽገው ከተማውን የፀረ አብዮት መስፈሪያ ባደረጉበት ጊዜ፤ በዚህ አዋጅ አማካይነት የከተማውን ሕዝብ ለማደራጀትና ጥቅሙን ለማስጠበቅ ተችለዋል::

2ኛ/ በቤት ኪራይ ይገኝ የነበረው ከፍተኛ ገንዘብ፤ ለፀረ አብዮት ኃይሎች መጠናከሪያ እንዳይውል ሆንዋል::

እንግዲህ ባጠቃላይ ደረጃ በዚህ ወቅት ውስጥ የተደረጉት ትግሎችና የተገኙት ድሎች እነዚህ ናቸው:: ከፍ ብለን ከዘረዘርነው ለንገነዘብ እንደምንችለው ከአማን አንዶም መውረድ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድረስ የነበረው ወቅት፤ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ድሎች የተቀዳጀባቸው ብቻ ሳይሆን የሰፊው ሕዝብ ትግል ለከፍተኛ የትግል ምዕራፍ መሠረት የጣለበትም ጭምር ነው:: በሌላ አነጋገር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች በኢኮኖሚ ደረጃ የተመቱበትና ከጠጋኝነት በከፊል ወደ ተቃዋሚነት የተሸጋገሩበት አዲስ የትግል በር የከፈቱ ጊዜ ነበር:: የዚህን ወቅት ታሪካዊ ፋይዳ በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል:: አለበለዚያ ግን በኢትዮጵያ ከ3 ዓመት ጀምሮ የሚካሄደው ትግል ለውጥ አላስከተለም፤ የሃይለ ሥላሴ ስርዓት ተቀጥሏል ነው ከሚሉት ፀረ ሕዝቦች ጎን በቀጥታ መሰለፍ ማለት ነው::

ከዚህም አልፎ የዚህን ወቅት ታሪካዊ ፋይዳ በሚገባ ካልተረዳን፤ ቀጥሎ ለሚመጣው ምዕራፍ ትክክለኛውን ትርጉም ልንሰጠው አንችልም:: ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ትርጉም፤ ትግሉ እንዴት ሊቀዘቅዝ ቻለ፤ ፀረ ሕዝብ ኃይሎችስ በምን ዘዴ ተጠቀሙ የሚሉትን ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ከፍ ብለን ያተትነውን የትግል ወቅት በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል::

## 3. የሁለት ወሩ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

ይህ አዋጅ ከታወጀበት ጊዜ አንስቶ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ አይሉ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ባለበት የረገጠበት ወቅት ነው:: ይህ ለምን ሊሆን ቻለ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ፤ ቀደም ብለን ከተነንነው የትግል ወቅት መነሳት አለብን ብለናል:: ለማስታወስ ያህል፤ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከመታወጁ በፊት በነበረት ወራት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የመጀመሪያዎቹን መሠረታዊ ድሎች ተቀዳጅተዋል:: በፀረ ሕዝቡም ወገን ያልተጠበቀ አብዮታዊ ማዕበል ረግፎበታል:: ለንገነዘበው እንደቻልነው፤ የቀድሞ ገዢ መደቦችም ሆኑ ኢምፔሪያሊስቶች ወደ ከፊል ተቃዋሚነት ይሸጋገሩ እንጂ በሚገባ ተደራጅው ኃይላቸውን አላሰባሰቡም ነበር:: በሌላ አነጋገር በጥቂት ወራት ውስጥ የተደረገው ፈጣን አብዮታዊ እርምጃ፤ በፀረ ሕዝቡ ወገን ለጊዜውም ቢሆን ሽብር ፈጥሮ ነበር ለማለት ይቻላል::

ይሁንና ይህ ሸበር ለዘላለም እንደማይቀይ ሳይታለም የተፈታ ነበር:: በድንገት በዙም ባይዘጋጁለት የመታቸው አብዮታዊ ማዕበል፣ አድሃሪያቸን እንደ ዲያሰባቸውና፣ ቸግራቸውንም ለመቋቋም የተበታተነውን ኃላቸውን ለመሰብሰብ እንደ ሚገፋፋቸው መገመት አያስቸግርም:: በተራማጁ በኩል ደግሞ፣ የነበረትን የድርጅት ጉድለቶች ስንመለከት፣ በተራማጅ ማህል የነበረውን የመስመር ትግል ስናስታውስና፣ስህተተኛው መስመር ቢያንስ በወጣቱ ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት ስንገነዘብ፣ አብዮታውያን የተበታተነን ፀረ ሕዝብ ሰፈር ለማሸበር በቂ ኃይል ይኑራቸው እንጂ፣ የተደራጀን ፀረ ሕዝብ ሰፈር ለመቋቋም በበቂ እንዳልተዘጋጁ ለመገመት አያስቸግርም:: እዚህ ላይ አንዳንዱ ነገሮች ማስታወስ ይጠቅማል::

—በመስከረም 1968 ዓ.ም በደሴ ከተማ " በኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት " የተደራጁት ፀረ ሕዝቦች ተሰበሰበው፣ ኃይላቸውን ለማስተባበር በአድሃሪ አረብ መንግሥታት እጋዥነት ከፍተኛ ውይይት ያካሄዱ::

—በዚሁ ሰሞን፣ በደርጉ ቀኝ ክንፍ ቀስቃሽነት ለባላባቶች ምህረት ይደረጋል::

—ትግላቸውን ወደፊት ለማራመድ ቆርጠው በተነሱ የገበሬ ማህበራት መሪዎቸና አብዮታዊ ዘማቾች ላይ መንግሥት ፀረ ሕዝብ እርምጃ ያስወስዳል::
ለዚሁ የነሰለሞን እኔ ምሳሌ በቂ ማስረጃ ነው::

—በደርጉ ቀኝ ክንፍ ቀስቃሽነት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይታወጃል::

—ኢምፔሪያሊስቶች ከመቼውም ይበለጥ፣ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ይዘምታሉ::

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያሳየው፣ ከፍ ብለን እንዳልነው፣ ፀረ አብዮት ኃይሎች የተበታተነው ኃይላቸውን ለመሰብሰብ እየተዘጋጁ እንደነበር ነው::

ይህ የፀረ አብዮት ሰፈር መጠናከር ብዙ ውጤቶች ማስከተሉ አልቀረም:: በመስከረምና በጥቅምት 1968 ውስጥ ብዙ ፀረ አብዮት ድርጊቶች ተፈጽመዋል:: በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ላይ ተኩስ ተከፍቶ ብዙ ንፁህ ደም ፈሰሰ፣ ብዙ ተራማጆች ተገደሉ...ወዘተ

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ሰዓት፣ በ"ዲሞክራሲያ" ስር የተሰበሰበው ከሃዲ ቡድን ፋሽስት ለሚለው አነጋገር "ማረጋገጫ" ያገኘ መስሎት ብዙ ደበደና እርምጃዎች በሠራተኛው እንዲወሰዱ በመገፋፋት፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ላይ ብዙ ግፍ እንዲፈጸም ገፋፍተዋል::



የእውነተኛ ተራማጆች እጅ ግን ፍፁም ለቁ ነበር:: ለዚህም የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 31 ን ማንበብ ይጠቅማል:: እናም በሰፊው እንጥቀሰው::

በየካቲት 1969 ዓ.ም ፈንድቶ ብዙ ድሎችን የተገናጸፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ተጋድሎ በአሁኑ ወቅት በርግጥ ባለበት ቆሞ በመርገጥ ላይ ይገኛል::.....ዛሬ ሰልፋቸውን እያሰመረ ከሄዱት አድሃሪያቸና የመሰንፍት ርዝራዦች በስተቀር የኢትዮጵያን አብዮት ወደፊት ለመግፋት የሚችሉት ኃይሎች በሙሉ ወሸንበር ባህር ውስጥ የሚዋኙበት ጊዜ ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም:: ከዚህ ወሸንበር ውስጥ ለመውጣት ተራማጁት ሁሉ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሃገሪቱዋን ተጨባጭ ሁኔታ ተንትነው በመረዳት ታክቲካቸውን መቀየስ አለባቸው:: ይህንንም ታክቲክ ለመቀየስ ሃገሪቱ የምትገኝበትን ታሪካዊ ወቅት፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉት መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ያላቸውን ግንኙነት፣ ዝምድናም ሆነ ቅራኔ ተንትኖ የያንዳንዱን መደብ አሰላለፍ ሁኔታ ማጤን እንደሚያስፈልግ ታላቁ ሌኒን ያስተምረናል:: ይህም ትንተና የሚደረገው ለቲዎሪ ቅንጦት ሳይሆን የጊዜውን ዋና ጠላቶች ከጊዜያዊ ወዳጆች ለመለየት፣ በጠላቶች ሰፈር ሊኖር የሚችለውን ቅራኔ በሚገባ ለማወቅና ይህንንም የግጭት ፍንጭ በማባባስና በማስፋት ጠቅላላውን የጠላት ሰፈር ለማዳከም፣ ጊዜያዊ ወዳጆች ሊሆኑ የሚችሉትን ደግሞ አረጋግተና አሳምሮ ወደአብዮቱ የሚስብ ታክቲክ ለመከተል እንዲቻል ነው::

ባጭሩ የሃቀኛ ተራማጆች መልከት፣ አድሃሪያቸ ከመሸበር አለፈው ኃይላቸውን ሰበሰበዋልና፣ አብዮታውያንም በዚሁ መጠን ኃይላቸውን ይሰብሰቡ የሚል መልከት ነበር::

በቀላል ልንረዳው እንደምንቸለው፣ ኢትዮጵያ በነዚህ ሁለት ወራት ውስጥ ከነበረችበት አስቸጋሪ ሁኔታ ለማውጣት ተራማጆች ብዙ ትጋትና ቆራጥነት አስፈልጿዋል:: እንደውነቱ ከሆነ፣ ዛሬ መለስ ብለን በነዚህ በሁለት ወራት ውስጥ ተራማጁ ግለሰቦችና ተራማጁ ድርጅቶች ያደረጉትን ተጋድሎና ያገኙትን ውጤት ስናይ፣ እውነትም ግዴታቸውን በሚያኮራ አኳኋን አሟልተዋል ለማለት ያስደፍረናል:: ምናልባትም፣ የኢትዮጵያ ተራማጆች በነዚህ በሁለት ወራት ውስጥ የተጠቀሙበት የትግል ዘዴ ያሳዩት ጥረት፣ በታሪክ እንደምሳሌ የሚጠቀስ ይሆናል::

ለማንኛውም ይህ የተደረገው ከፍተኛ ትግል ውጤት ማምጣቱ አልቀረም:: የአብዮቱ ሰፈር ከሞላ ጎደል ሊጠናከር በመቻሉ፣ ለሁለት ወር የቆየው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተነሳ:: ከዚያም በተከታታይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የማይናቁ ድሎች ሊቀዳጁ ችለዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል እንደገና አዲስ የድል ምዕራፍ ውስጥ ሊገባ ችለዋል እንላለን::

እናም ወደ አራተኛው ክፍል እንዘዋወር::

4. ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መነሳት እስከ ተፈሪ በንቲ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍ

እንግዲህ ይህ ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀው ፀረ ሕዝቡ ክፍል ከድንጋጤው ወጥቶ ራሱን አደራጅቶ ቀና ቀና ማለት በጀመረበት ወቅት እንደሆነ ሁሉ፣ ተራማጆች ደግሞ ራሳቸውን አስተባብረው አዋጁን ማስነሳትና ትግሉን ወደ አዲስ የድል ምዕራፍ አስገብተውታል ብለናል:: ስለዚህም ከዚ በኋላ የሚካሄዱትን ትግሎች አይነተኛ የሚያደርጋቸው፣ በጠላትም ሆነ በሕዝብ ዘንድ በመጠኑ በተደራጀ መልክ የተካሄዱ ትግሎች መሆናቸው ይሆናል:: የትግሎቹን ይዘት ለመመርመር እንሞክር::

ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንደተነሳ፣ ስለ ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ወጣ:: ይህ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ጉድለቶች እንዳሉት ተደጋግሞ ተነግሯል:: ከጉድለቶቹም አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል::

የሥራ ማቆም መብትን አያውቅም፣ ሥራ ለማቆም ከ80 ቀን በፊት ማስታወቅ ያስፈልጋል፣ ራሱ አዋጁ በሚገባ አልተፃፈም ስለሆነም ለቢሮክራሲው አሻጥር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል::
እነዚህ ጉድለቶች መሠረታዊ ጉድለቶች ናቸው:: ተራማጆችና ተራማጅ ድርጅቶች በጊዜው አጋልጠዋቸዋል:: ይሁንና የአዋጁ መታወጅ ተዘግቶ የነበረውን የሠራተኞች ማህበር ባዲስ መንፈስ ለማቋቋም፣ ከፍተኛ የትግል መድረክ መክፈቱ አልቀረም:: አብዮታውያን፣ ጉድለቶቹን ያጋለጡትን ያህል በአዋጁ ተጠቅመው የሠራተኛውን ማህበር ባዲስ መንፈስ ለማቋቋም የተነሱት በዚን ወቅት ነበር:: ለብዙ ዓመታት የሠራተኛውን ማህበር ከፀረ ሕዝቡ አመራር ለማፅዳት የተደረገው ጥረት በዚን ጊዜ መልክ ይዞ ሊካሄድ ችሏል:: የፀረ አብዮት ኃይሎች በተለይም የንዑስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ ይህንን ጥረት ለማደናቀፍ "አትደራጁ ታገሉ" የሚለውን መፈክር ማንገቡ ይታወሳል:: ሆኖም ግን ተጋለጠበት እንጂ፣ ሠራተኛው በዚህ በተሳሳተ መፈክር ስር አልተሰለፈም:: ዛሬ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር /መኢሠማ/ መቋቋም ለዚህ በቂ ምስክር ነው::

ከዚም ሚያዝያ 12 የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ወጣ፣ ዛሬ መለስ ብለን ይህ ፕሮግራም የወጣበትን ጊዜ ስናስታውስ፣ ባንድ በኩል ፀረ ሕዝቡ ክፍል ከኢምፔሪያሊስቶች አንስቶ እስከ ታላላቅ ነጋዴዎች ድረስ፣ ከባላባቱ እስከ ንዑስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ ድረስ በየረድፉ አብዮቱን ለመቀልበስ ሲቀሳጠፉ፣ በሌላው በኩል የአብዮቱ ክፍል ራሱን ሲሰበስብና፣ በደርግም ውስጥ የግራው ክንፍ አብዮቱን ለማራመድ ጥረት ሲያደርግ እንደነበር ስንገነዘብ፣ የዚህ ፕሮግራም መውጣት ለሕዝቡ ትግል ምን ያህል አመቺ ሁኔታ እንደፈጠረ ለመረዳት አያስቸግርም::



የዚህ ፕሮግራም መውጣት፣ ተራማጆች በግልጽ ለነፃ ለተደራጀና ለታጠቀ የሕዝብ ትግል ቅስቀሳ እንዲያደርጉ በር ከፍቶላቸዋል::
ለምሳሌ በ፤ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ወዘተ... ስለ ኢትዮጵያ ትቅደም፣ ስለ ኢትዮጵያ ሶሻሊዝም፣ ስለ አንድ ብሔራዊ ፓርቲ በሰፊው ይጻፍ እንደነበር እናስታውስ:: የዚህ ፍልስፍና ውጤት ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተከከለናው የትግል መስመር ማራቅ እንደነበር ለመገመት አያስቸግርም:: እርግጥ "ሕብረተሰባዊት የመንግሥት መምሪያ መሆኑ፣ ሰፊውን ሕዝብ የሃይለ ስላሴ የጭለማ ዘመን ለማውጣት በመጠኑም ቢሆን ረድቶዋል:: ነገር ግን ይህ መመሪያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጭቆና ሊያወጣ እንደማይችል ግልጽ ነው:: ገፋ ብሎ በሶማሊያ ወይንም በታንዛንያ እንደታየው በሶሺያሊዝም ስም ቢሮክራቲክ ከበርቴው ስልጣኑን ይዞ ይቀይ ነበር እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕዝባዊ ስርዓትን በዚህ መመሪያ ስር ሊገነባ አይችልም ነበር:: እንግዲህ ይህ የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ከመውጣቱ በፊት፣ ተራማጆችና ተራማጅ ድርጅቶች ለዘላቂው ትግል የሚያደርጉትን ቅስቀሳ በነፃ ጋዜጦችና በስውር ትግል መወሰን ነበረባቸው ማለት ነው:: ፕሮግራሙ ከወጣ በኋላ ግን የቅስቀሳ መድረካቸው እስከ መንግሥቱ ጋዜጦች ድረስ ሊዘረጋ ችሏል:: በራሱ በመንግሥቱ ጋዜጣ፣ ደርግ በሕዝብ ስርዓት እንዴት ሊተካ እንደሚችል ሰፊ ቅስቀሳ ማድረግ ተችሏል::
ከዚም አልፎ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እንዴት ሊነቁ እንደሚችሉ፣ በጥናት ክበብ በውይይት ክበብ መደራጀት እንዳለባቸው በግልጽ መናገር ተችሏል:: እንዲሁም በድርጅት በኩል የወዛደሩ ፓርቲ እንዴት መደራጀት እንዳለበት፣ ያንድነት ግንባር እንዴት መቋቋም እንዳለበት በመንግሥቱ ጋዜጦች ከመቀስቀስ አልፎ የነዚህን ድርጅቶች ጽንስ በግልጽ ለማቋቋም ተችሏል:: በዚህም ሳቢያ ስለ ሰፊው ሕዝብ መታጠቅ አስፈላጊነት በፕሮግራሙ በመመርኮዝ ሰፊ ቅስቀሳ ለማድረግ ተችሏል::

የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ከወጣ በኋላ የመንግሥቱ ጋዜጦች የዜና ማሰራጫዎችና፣ ህጋዊ ጋዜጦች መስመር ቀይረዋል ለማለት ይቻላል:: ይህም ከፍተኛ ምዕራፍ ነበር::

የዚህ ፕሮግራም ሌላኛው ዋና ነጥብ የብሔርን ጥያቄ የሚመለከተው ነበር ለማለት ይቻላል:: ለመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት ደረጃ የብሔሮችን እኩልነትና የብሔሮችን መብት የሚያውቅ መመሪያ መውጣቱ ትልቅ ድል ነበር:: እርግጥ ይህ መብት በሪጅናል አቶኖሚ በወሰንም፣ መንግሥት ይመራበት በነበረው ትምክተኛነት አንፃር ሲታይ አንድ የማደናቀ እርምጃ ተደርገዋል::

እንግዲህ እነዚህ የዘረዘርናቸው ነጥቦች ብዙ የተገለ ውጤቶችን እንደ ሚወለዱ ለመገመት አያዳግትም ነበር::

ከሚያዝያ 12 ፕሮግራም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብዙ ድሎች ተቀዳጅተዋል::

ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው በግንቦት 8 የኤርትራን ችግር በሰላም ለመፍታት የተሰጠው የፖለቲካ ውሳኔ ነው::

ከፍ ብለን የኢትዮጵያ አብዮት ለመቀልበስ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ስንዘረዝር፣ የኤርትራን ነጥብ አንስተን ነበር:: ኢምፔሪያሊስቶች የኤርትራንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አያያዥ አብዮታዊ እንቅስቃሴውን ለመቀልበስ ታጥቀው እንደተነሡ አይተናል:: ስለሆነም፣ ተራማጆች ባይታክቱ የኤርትራ ጉዳይ በሰላም እንዲፈታ ቅስቀሳ አድርገው ነበር:: የግንቦት 8 ውሳኔ ከመውጣቱ በፊት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በኤርትራ ላይ ሰራዊት ለማዘመት የወሰነው በነዚሁ በቀኝ ኃይሎች በመገፋፋት ነበር:: በዚን ጊዜም መላ ተራማጅ ይህን ፀረ ሕዝብ ዘመቻ ተቃውሞ ተነስቶ በግንቦት 8 የሰላሙ ውሳኔ ሲወጣ ለተራማጆች ከፍተኛ ድል ነበር ማለት ነው:: ከዚህ ውሳኔ በኋላ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ከተሞች እንዲሁም በአስመራ የተደረጉት ሰልፎች የጭቁኖች አንድነትን በሚገባ በማንፀባረቃቸው ትምክህተኛነትና ጠባብ ብሔረተኝነት ለኢትዮጵያ ሕዝቦች እንደማያዋጡ በሚገባ መገንዘብ ተችሏል:: ሕዝብም በሚገባ ተገንዝቦታል::

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሳት በኋላ የወጡት የመንግሥት መመሪያዎች፣ እንዲሁም ደግሞ ታህሣሥ 3 ቀን የገበሬዎችን ማህበራትን ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ተከታትለው የመጡ የሰፊው ሕዝቦች ድሎች ናቸው:: ይህም ሊሆን የቻለው ከፍ ብለን እንዳልነው ተራማጆች ለአብዮት የሚሰለፉ ኃይሎችን የደርግ ግራ ክንፍን ጥምር ባንድ ለማስተባበር ባደረጉት ጥረት ነው::

እነዚህ ድሎች በገጠር ብዙ አዳዲስ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠላቶች በትክክል ጠቁሞ ለማጥቃት በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ንቃትን የተሻለ ድርጅትን የተጠቀን ቀዝማ አስከትለዋል:: ለምሳሌ ያህል በቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴው ክፍል በወጣቱ በሠራተኛውና በምሁራን ዘንድ የተሰራጨውን ፀረ አብዮት አስተሳሰብ ለማጋለጥ ተችሏል:: ትክክለኛው መስመር በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሆኗል:: በድርጅት በኩል አብዮታዊ ድርጅቶች በየቦታው ከመፍለቃቸውም ሌላ እነ መኢሶን በበለጠ አቀፍ ደረጃ እየጠነከሩ መተዋል::



ገበሬ ማህበራት በየቦታው ሲጠናከሩ በገጠር የጥበቃ ጓዶች በየቦታው ሲቋቋሙ በተጠር የሚገኘው ቢሮክራሲ ሚናው በከፊል ተቀንሶ ታይቷል:: እንዲሁም በከተማ የቀበሌ ማህበራት ተቋቁመው፣ የከተማውን አስተዳደር በከፊል በእጃቸው በማስገባታቸው፣ የሕብረት ሱቆች ትምህርት ቤቶች ወዘተ በመክፈታቸው የነጋዴውን አሻጥር በከፊል መቋቋም ተሞክሯል::

እርግጥ በትጥቅ በኩል ተጨባጭ ውጤት ባይታይም፣ በሃሳብና በቅስቀሳ ደረጃ በሚገባ በመስፋፋቱ ሰፊው ሕዝብ ለትጥቅ የሚያደርገውን ትግል በጥፍ ድርብ ሊጨምረው ችሏል:: ይህ ሁሉ መሆኑ የፀረ አብዮትን ክፍል እንዲያሸማቅቀው በወቅቱ በሚገባ ይታይ ነበር:: ነገር ግን ፀረ ሕዝቡ ክፍል ያም ቢሆን ክፋ አላቋረጠም:: በልዩ ልዩ ዘዴዎች የኢኮኖሚ አሻጥር፣ ሽብር ፈጠራ...ወዘተ ሁኔታውን ለቀልበስ ሲያመቻች በመንግሥት ደረጃ መፈንቅለ መንግሥት በመጠንሰስ ተሰማርቶ ነበር:: በሐምሌ 68 ገደማ ይህ ሁኔታ የበሰለ መሰሉ ነበር ለማለት ይቻላል::

በተራማጁ ዘንድ ምንም እንኳ ከፍተኛ ድሎች ቢገኙም፣ በየፈናው አገሪቱን የወጠርዋት ሰው ሰራሽ ችግሮች መውጫና መግቢያ ያሳጡት ይመስል ነበር::

የሲሳይ ሀብቴ፣ ጌታቸው ናደው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የመጣው ከፍ ብለን የጠቀምነው ሁኔታ እያለ ነው:: በዚህ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ውስጥ የዋሞያች መሳተፍም፣ በሁለት መስመር ማህል በተደረገው ትግል ትክክለኛው መስመር ድል እየመታ ከመሄዱና የፀረ ሕዝቡን መስመር ሕዝባዊ መሰረት ከማሳጣቱ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም:: እዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ነጥቦች ማስታወሱ ይጠቅማል::

ከብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም በኋላና ከትቂት ጊዜ በፊት ፀረ ሕዝቡ ክፍል በልዩ ልዩ "የትግል ዘዴዎች" በመሠማራት በጠቅላይ ደረጃ ሲታይ አገሪቱ ውስጥ ሽብር ለመፍጠር ከዛም መፈንቅለ መንግሥት ለመጠንሰስ እንደ ተሰማሩ አይተናል:: ይህም "የትግል ዘዴ" በይበልጥ መታየት የጀመረው የደርጉ ወደ ቀኝ መንሸራተት /ለምሳሌ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ስም/ በተራማጆች ሊገታ ከቻለ በኋላ መሆኑን ተገንዝበናል:: እዚህ ላይ መረዳት የሚያስፈልገው፣ ይህ ከፍ ብለን የጠቀስነው "አዲሱ የፀረ ሕዝቦች የትግል ዘዴና አላማ" አድሃሪውን ክፍልና በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ስር የተሰለፈውን የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ በይበልጥ እንዳቀራረባቸው ነው:: ይህ "የትግል ዘዴና የዓላማ" መቀራረብ በቅርብ በገቢር እንደሚተረጎም ባይታለም የተፈታ ነበር:: በተለይ የቀኝ ክንፉ ንዑስ ከበርቴው መጋለጥ፣ በዛኑ ሰሞን ለምሳሌ የዘመቻው በተካካ መንገድ መካሄዱ፣ ይህንን "የሥራ ትብብር" እንደሚያፋጥነው መገመት ይቻል ነበር::

•• የተፈራው •• አለ ቀረም የኢትዮጵያን ሕዝቦች መንቃት መደራጀትና መታጠቅ በገ በገቢር መቃወም የጀመረው በኢህአፓ የሚመራው ቡድን፣ በግልጽ ከሲ.አይ.ኤና በሲሳይ ጋር በመፈንቅለ መንግሥት ተሳተፈ:: ስለሆነም የነሲሳይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ በሁለት መስመር ማሀል በሚደረገው ትግል አንፃር ሲታይ አዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል ለማለት ይቻላል:: በሌላ አነጋገር •• ጊዜአዊ ሕዝባዊ መንግሥት•• የሚለው መፈክር የመፈንቅለ መንግሥት መፈክር ወደ መሆኑ የተሸጋገረበት ወቅት ነው::

በናስታውሰ፣ የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም እንዲታወጅ፣ ኢህአፓ •• ዲሞክራሲያ•• በተባለው ልሳኑ አማካይነት፣ በለዚሁ ጉዳይ ባወጣው ልዩ እትም ዉንገት ከደርግ ጋር ግንባር ለመፍጠር ጥሪ አድርጉ ነበር:: በዛን ጊዜ ተራማጆች ገሩ የገባቸውን ያህል፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የነሲሳይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሲጋለጥ፣ በኢህአፓ የተደረገው የግንባር ጥሪ ትርጉም ጊዜአዊ ሕዝባዊ ደርግ ከነሲሳይ ደርግ ጋር ለማቋቋም እንደሆነ ተራማጆ ሊረዱ ችለዋል:: መፈንቅለ መንግሥቱ ሊከናወን ሰሞን ኢህአፓ በዉንገት የሥራ ማቆም ጥሪ ወዘተ... ያደረገውም ባጋጣሚ አልነበረም:: በነገራችን ላይ ከዚ በኋላ የከሸፉት መፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ሁሉ እንዳሳዩት፣ መፈንቅለ መንግሥቶች በታቀዱ ጊዜ ሁሉ ኢህአፓ የሥራ ማቆም ጥሪ በማድረግ የተፈለገውን ሽብር ለመፍጠር በግንባር ቀደምነት ተሳትፈዋል:: ወደ በኋላ እንመለስበታለን:: የሲሳይ መፈንቅለ መንግሥት ፀረ ሕዝብ ክፍል በሰፊው ያስተባበረ ነበር:: ቀደም ሲል ታላላቅ ነጋዴዎች በከፍተኛ ደረጃ ያካሄዱ የነበረው የኤኮኖሚ አሻጥር ከዚሁ ተነጥሎ አይታይም:: በዚሁ ሰሞን የአሜሪካን የጦር መርከቦች በአሰብ አካባቢ ማንዣበባቸው ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጋር የተያያዘ ነው:: መፈንቅለ መንግሥቱ ከከሸፈ በጥቂት ቀናት በኋላ በአየር ወለድ ወታደሮች በደብረ ዘይት አካባቢ የተፈጠረው ውዝግብ ከዚም የሲሳዩ ከሶኔል ብርሃኑ ሃይሌ ሙከራ ከነሲሳይ መፈንቅለ መንግሥት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ይቻላል:: እንዲሁም ኮሎኔል ብርሃኑ ኃይሌ ከአሜሪካን የጦር መርከቦች ጋር ግንኙነት ያደረገ እንደነበር ለመገመት ይቻላል::

የሆነው ሆኖ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ከሸፈ:: አሻጥረኛ ነጋዴዎቹ ላይ ጥምር አብዮታዊ እርምጃ ተወሰደባቸው::

የዚህ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍ አንዳንድ ነገሮችን ለመረዳት አስችሏል:: ይሁን እንጂ ያገሪቷን ሁኔታ በመሠረቱ ለውጧል ለማለት አይቻልም:: ለምሳሌ የአየር ኃይል ወታደሮች ከአየር ወለድ ጋር አንተባበርም ማለት፣ እንደዚሁም የኮሎኔል ብርሃኑ ሃይሌ በራሱ ባልደረባ በቃች መገደል፣ ከወታደሩ ማሀል ለአብዮቱ ቆርጦ የተነሳ ክፍል እንዳለ አስገንዝቧል::



ነገር ግን ያገሪቷ ሁኔታ በመሠረቱ አልቀየረም ያልንበት ምክንያት፣ አንደኛ ተራማጆች ድል ቢቀዳጁም አገሪቷን የወጠራትን ችግር የኑሮ መወደድ፣ የሠራተኛ ደመወዝ ማነስ ወዘተ... ለመቋቋም አስቸጋሪ ሁኔታ መኖሩ አልቀረም:: ሁለተኛ፣ ፀረ ሕዝቡ ክፍል የነሲሳይ ሙከራ ቢከሸፍም •• ሲሳይ ቢሄድ ተፈሪ ይመጣል•• የሚል ግምት ያለው ይመስል ነበር:: በሌላ ደረጃም የኤኮኖሚ አሻጥሩም ሆነ፣ ሽብር ፈጠራውን አሳምሮ ለመቀጠል ዝግጁ መሆኑ አልቀረም::

አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተነሳ ወዲህ ባንድ በኩል ተራማጆች ድል እየተቀዳጁ ኃይላቸውን ሲሰበስቡ፣ በሌላ በኩል ፀረ ሕዝቡ ክፍል ሲያሻጥር መፈንቅለ መንግሥት ሲጠነስስ ሽብር ሲፈጥርና ተራማጆችን ሲያፋጥጥ 1968 ዓ.ም ከፍጻሜ ደረሰ:: በግራም ሆነ በቀኝ የተሰለፈው ኃይል፣ መስከረም ሁለት ላይ መፋታትን ነበረበት መፋታቱም አልቀረም::

መስከረም ሁለት 1969 በማያዳግም ሁኔታ ለተራማጆች ድል ሆኖ ውሏል:: ከዚም አልፎ መስከረም ሁለት የሕዝቡንና የፀረ ሕዝቡን ክፍል ጥርት ባለ ሁኔታ ለይቶ አሳይቷል::

መስከረም ሁለት ለተራማጆች የኃይላቸው ምልክት የሆነው ያህል ደግሞ፣ ለአድሃሪያት የድክማቸው ምልክት ስለሆነም ማስጠንቀቂያ ነበር::

ተራማጆች ከድላቸው ተነስተው በይበልጥ ለመጠናከር ተበፋ እንዳደረባቸው ሁሉ፣ ፀረ ሕዝቦች ከበረታቸው ተነስተው ከስህተታቸው በመማር • ትግላቸው•• ከፍ ባለ ደረጃ ማካሄድ እንዳለባቸው ተረድተዋል ለማለት ይቻላል:: <u>ስለዚህም ከመስከረም በኋላ በሁለቱ ክፍል ማሀል የሚካሄደው ትግል በይበልጥ የረቀቀና የከረረ እንደሚሆን አያጠራጥርም ነበር::</u>

መስከረም ሁለት ካለፈ ከጥቂት ቀናት በኋላ በሻለቃ መንግሥቱ ላይ የረቀቀ የግድያ ሙከራ ተካሄደ:: እንደሚባለው ከሆነ፣ ይህ ሙከራ በተካሄደበት ወቅት ገዳዮቹ የተጠቀሙበት መሳሪያ በቁጥርም ሆነ በዓይነት በቀላሉ የሚገመት አልነበረም:: ከዚም በበዙ ጓዶች ላይ የሞት አደጋ ተጣለባቸው:: እነ ጓድ ፍቃሬ፣ እነ ጓድ ገብረ እግዚአብሔር ተገደሉ:: ሌሎችም በየበታው ተመሳሳይ አደጋ ገጥሟቸዋል:: በተለይ በታህሣሥና በጥር ወር በቀበሌ ማህበራት መሪዎችና ከተራማጅ ተማሪዎች ማሀል በመቶ የሚቆጠሩ ተገደሉ::

አርግጥ በደርግ በኩል ይህን አሻጥር በፈጸሙት ላይ ከገኛም ሁለቱም የሞት ቅጣት ተፈጸመባቸዋል:: ተራማጅ ድርጅቶች በበኩላቸው ባገዱ በኩል ይህንን ጥቃት ሲቋቋሙ፣ ባደረጉት ከፍተኛ ትግል ከሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት በማትረፍም ሆነ ትግሉን ተከከለና ተቀጣጣ በማያስያዝ ብዙ ዉሎችን ተቀዳጅተዋል:: የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር መቋቋም፣ የቀበሌ ማህበራትን ለማጠናከር አዋጅ መዉጣት፣ የትራንስፖርት ደንብ መታወጅ፣ ትምህርት ቤቶች በቀበሌና በገበሬ ማህበራት ቁጥጥር ስር መዋላቸው፣ ገንዘብ መለወጡ...ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የማይናቁ ድሎች ናቸው::

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ብዙ ግለጽ ያልሆኑ ሁኔታዎች ይታዩ ነበር:: በሻለቃ መንግሥቱ ላይ የረቀቀ የግድያ ሙከራ ተደርጎ፣ ለግድያ ሙከራው ያገለገሉት መሣሪያዎች ፍፁም የረቀቀ መሆናቸው አውቀ ሆኖ ሳለ፣ በዚህ ግድያ የተሳተፉት ሰዎች ለማስያዝም ሆነ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰዱ አስፈላጊው ጥረት የተደረገ አይመስለም:: 23 ሰዎች ላይ እርምጃ በተወሰደ ጊዜ ከማህላቸው ሻለቃ መንግሥቱን ለመግደል የሞከረት ይገኙበታል ተብሎ ታለፈ:: በመንግሥት ደረጃ ይህ ነገር ታፍኖ ያለፈ ይመስል ነበር::

የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 51 ስለዚህ ወቀት ሲያወራ እንዲህ ይላል:: የሬድዮው የትዝታ ዘፈኖች የበርከራሰው አንደገና በየቦታው ቁና ቁና ማለት የኢ.ዲ.ዩ. መጠናከርና የኢህአፖ የነፍስ ገዳይነት ድርጊቶችን ማፋፋም እነዚህ ሁኔታዎች ባንድነት ተደማምረው ለሰፊው ሕዝብ በቂ የቀሰበሰ ምልክቶችን ሰተውት ነበር::"

ከዚህም አልፎ ሌሎች ግለፀ ያልሆኑ ሁኔታዎች ነበሩ:: እነ ተስፋዬ ታደሰን ከፍሌ ወዳጅን የመሰበሉ፣ ፀረ ሕዝብነታቸው ያደባበይ ሚስጥር የሆነው ለምን ከፍተኛ ቦታ ይዘው እንዲቆዩ ሆነ:: እንዲውም ተስፋዬ ታደሰ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ባለው ቦታ በመጠቀም፣ በጋዜጣ ላይ ኢህአፖን የሚያወግዝ ጽሑፍ ወይም ዜና እንዳይታለፍ ተፅኖ ያደርግ እንደነበር በደንብ ይታወቃል::

ከሁሉ ይበለጥ ተራማጆችን ግራ ያጋባው ግን በደርግ ውስጥ የተደረገው የሥልጣን አከፋፈልና በደርጉ የበስተ አካሌች መደራጀት ነው:: በደርጉ አሰራር ውስጥ አናርኪ ተፈጥሮ፣ የደርጉን አሰራር ማስተካከል አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ፣ ነገሩ አስደናቂ ባልሆነ ነበር:: ነገር ግን ይህ ነጥብ እንዴት ይገገተኛ መፍትሄ አስፈለገው ለምንስ ለሌ/ቀ መንበሩ አጥፍ ድርብ ሰለጣን ተሰጣቸው:: ለምንስ የሕዝብ ድርጅት ጊዜአዊ ጽሕፈት ቤትን በደርጉ ማዕከላዊ ኮሚቴ ቁጥጥር ስር ማድረግ አስፈለገ:: እነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙት በዚህ በአዲስ የሥልጣን ከፍፍል የተጠቀመው የደርጉ የትኛው ክንፍ ነው የሚለውን ጥያቄ ስንመልስ ነው::



የነአለማየሁ ሃይሌ የደርጉ ዋና ፀሐፊ መሆን/በነገራችን ላይ ይህ ዋና ፀሐፊ የሚለው ሥልጣን ለአለማየሁ ተብሎ የተፈጠረ ይመስላል/ የነሞገስ መጠናከር፣ የነ ሻለቃ መንግሥቱ ስልጣን መቀነስ የሕዝብ ድርጅት ጊዜአዊ ጽሕፈት ቤት ስልጣን መቀነስ የሚያሳየው ባዲስ የስልጣን አከፋፈል የደርጉ ቀኝ ክንፍ እንደ ተጠናከረ ነው::

<u>የሆነው ሆኖ፣ ከመስከረም ሁለት በኋላ በአንድ በኩል ተራማጆችና ተራማጅ ድርጅቶች ከሰፊው ሕዝብ ዘንድ እየተዋሃዱ፣ ድል እየተቀዳጁ በመጡም በሌላ በኩል በመንግሥት ደረጃ ከፍተኛ ቦታ የያዙ ፀረ ሕዝቦች ራሳቸውን እንደደራጁና እንዲሰበሰቡ በሥልጣናቸው በመጠቀም እየተጋገዙ የፀረ አብዮትን ክፍል እንዳገዙ ለመረዳት ይቻላል::</u>

ለማንኛውም ለዚህ ለተዛባ ሁኔታና ከፍ ብለን ለዘረዘርናቸው ግልፀ ያልሆኑ ነጥቦች በግልፀ መልስ ሊገኝ የቻለው ከጥር 20 ገደማ በኋላ ስለሆነ ይህንን ወቀት ጠጋ ብለን እንመርምረው::

ይህ ከፍ ብለን የተመለከትነው ሁኔታ ሰፍኖ ባለ፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና ተራማጆች የሁኔታውን አደገኛነት ተረድተው አብዮታዊ እርምጃ ለመውሰዱ ጊዜአቸውን ይጠብቁ እንደነበር ለመገመት አያስቸግርም:: ለአሁኑ ጥር 22 የተዘጋጀው ሰልፍም በዚህ መንፈስ የታቀደ ለመሆኑ ብዙ ማረጋገጫዎች ይገኛሉ:: በተለይ በሰልፉ ለት፣ የተያዙት መፈክሮች የመኢሰማ፣ የቀበሌ ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራትና የሕዝብ ድርጅት ጊዜአዊ ጽሕፈት ቤት ወኪሎች ያደረጉት ንግግር ለዚህ በቂ ምስክሮች ናቸው:: በአሁኑ ሰልፍ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በ በመንግሥት ደረጃ የተሰገሰጉት ፀረ ሕዝቦች ለማጋለጥ ቆርጠው ተነስተው ነበር:: የሆነው ሆኖ አሁኑ ጥር 22 ሰልፉ ሊደረግ ቀዳሚ ጥር 21 ማታ የቀደሞው ሊቀ መንበር ንግግር ያደርጋሉ:: ለምን በድንገት ንግግር አደረጉ፣ ንግግር እንዲያደርጉስ ማን ጠየቃቸው ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት፣ አንደኛ የሳቸውን ንግግር ይዘት መመርመርና የንግግሩን ይዘትና የሰላማዊ ሰልፉን መንፈስ ማነፃፀር ይጠቅማል:: ለማንኛውም የቀደሞው ሊቀ መንበር ሊያሰልፉት የፈለጉት መልዕክትና ሰፊው ሕዝብ ሊያሰማው የፈለገው ድምፅ ሰማይና ምድር እንደሚሆን የቀደሞው ሊቀ መንበር ራሳቸው አስቀድመው የተረዱ ይመስላል:: ስለዚህም ባይ ቀደሙን ለቀደማቸው፣ ቀደሚ ንግግር አድርጉ አሁኑ ሕዝቡ ቢሰልፍ እኔን ለመደገፍ የተደረገ ይመስለለኛል፣ የሚል ገምት አድርገባቸው ቀዳሚ ለት ማታ እንደ ዝብ እላ ንግግንቸውን ያደርጉ ይመስላል:: ንግግሩ ቀዳሚ ማታ ተደርጉ አሁኑ ጥዋት የወጣው በቋሚ ተጠርጣሪው ተስፋዬ ታደሰ ቁጥጥር ስር የወደቀው አዲስ ዘመን ሲጽፍ "ብርጋዴር ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ የጊዜአዊ ወታደራዊ ሊቀ መንበር በትንተናው ምሽት ያደረጉትን የቡሩራዊ ጥሪ ንግግር በመደገፍ ሕዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ከያቀጣጣው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት በዛሬው ቀን ይህንኑ ሰልፍ ለማድረግ የተፈቀደ መሆኑን አንድ የደርጉ ቃል አቀባይ አስታውቃል::" ይላል::

እዚህ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች ለማቅረብ እንገደዳለን:: የቀድሞው ሊቀ መንበር ንግግራቸውን ለሕዝብ ያሰሙት ቀዳሚ ማታ ነው:: እኚህ ዘመኑ የወጣው እሁድ በማለዳ ጥዋት ነው:: እንግዲህ ጥያቄው የሚቀጥለው ይሆናል:: ሕዝቡ ከመቼው ንግግራቸውን ሰምቶ ከመቼው የድጋፍ ሰልፍ በማግሥቱ ለማድረግ አቀደ? ይህ ሁሉ“ ከያቅጣጫው የመጣው ጥሪ” በቀዳሚ ለሊት ውስጥ ነውን? ያንን የመሰለ ሥነ ሥርዓት ያዘለ ሰልፍ የተዘጋጀው ባንድ ሌሊት ውስጥ ነው ወይ?

በበኩላችን መልሱ ቀላል ይመስለናል:: አንዳንድ የደረሱ ዜናዎች እንደሚገልፁት፣ ሰልፉ የታቀደው ከቀድሞው ሊቀ መንበር ንግግር በፊት ነበር:: ከንግግሩ በኋላ አልነበረም፣ ሊሆንም አይችልም:: ስለሆነም የቀድሞውን ሊቀ መንበር ንግግር “በመደገፍ” አይደለም ሊሆንም አይችልም:: እንዲሁም የቀድሞው ሊቀ መንበር እሁድ ሰልፍ መደረጉን አውቀው ቀዳሚ ንግግር ቢያደርጉ፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር አጋፋሪያቸው ተበፋቂ ታደሰ፣ እሁድ ለት በሚወጣው ጋዜጣ ላይ ከፍ ብለን የጠቀስነውን መልዕክት እንዲያስተላልፍ ስምምነት የተደረገ ይመስላል:: ስለዚህም የእሁዱ ሰልፍ በኢትዮጵያ ተራማጆችና በመንግሥት ደረጃ የተሰገሰጉ አድሃሪያች የተጋጨበት አንጂ ለማሰመን እንደሚፈለገው ሕዝቡ በርጉ ገበቸን የደገፈበት ሰልፍ አልነበረም::

የሆነው ሆኖ የቀድሞውን ሊቀ መንበር ንግግር ጠጋ ብለን እንመልከት:: እዚህ ላይ የቀዳሚው ማታን ንግግር ብቻ ሳይሆን በእሁዱ ሰልፍ ላይ የቀድሞው ሊቀ መንበር ያደረጉት ንግግርም ጥምር መመልከቱ ይጠቅማል:: ሰውዬው ለማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት በሁለት አጠቃላይ ነጥቦች ሊቋጠር ይችላል::

<u>አንደኛ</u>፣ ሰውዬው ሊያሳምኑን የፈለጉት፣ የጊዜው የኢትዮጵያ ዋና ጠላት ከውጭ ኃይሎችና ከአካባቢ አገሮች የሚመጣውና የመጣው ጥቃት መሆኑን ነው:: በቀዳሚ ማታው ንግግራቸው የሚቀጥለውን ይላሉ::“:....ጠላት ገፍቶ ሰመጣ /የውጭ ጠላት ማለታቸው ነው/ በአንድነት ላንድ ዓላማ መቆማችን ተደጋግሞ ሊፃፍ የሚችል መሆኑን ጠላቶቻችን ዘራም ጠንቅቀው ሊገነዘቡት ይገባል” ይላሉ:: በማግሥቱ እሁዱ ጥር22 ባደረጉት ንግግር ቀጠል አድርገው በዚሁ መንፈስ “ <u>በእሁኑ ጊዜ</u> አገራችንን <u>ከወራሪ ጠላት</u> ለመጠበቅና ከውጭ ተንኮለኞችን ለመከላከል ህብረት አጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ቀደም ብቶ አንደ ተናገርኩት በልዩ ልዩ ቡድኖች መካከል ቅራኔ ሊኖር ይችላል:: ይህም ቅራኔ ያገርን አንድነት ለመጠበቅ የሚከለከል ሳይሆን እርስ በርስ የሚደረግ ቅራኔ ነው:: በለዚህ በዚህ ቅራኔ ምክንያት አገራችን ለጥቃት እንዳትጋለጥ ጥቀኝ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን ማጠንከርና ሕብረቱንም ማበረታታት አለበት” ይሉናል::/በርዝ የተጨመረ/



<u>ሁለተኛው</u> መልዕክት ከዚሁ ጋር የተያያዘና ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ብሔራዊ ፖርቲ መቋቋም እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው:: የቀድሞው ሊቀ መንበር በእሁዱ ንግግራቸው፣ “ ሕብረት ብለን ብዙ ጊዜ ስንናገር፣ ልዩ ልዩ አቋም ያላቸው ክፍሎች ወይም ቡድኖች ተባብረው <u>አንድ</u> ፖርቲ አቋቁመው ተራማጅ ኃይላቸውን በሙሉ ሰብስበው፣ አገራችንን <u>ከውጭ ጠላት</u> መጠበቅ፣እንዲሁም አብዮታችን ከግቡ እንዲደርስ መንከባከብና ወደፊት መምራት ነው::....ባለፋት ሁለት ዓመታት ተኩል ጊዜ ውስጥ የዚህ አይነቱ በጥበቅ ታስቦበትና ተስርቶበት ቢሆን ኖሮ ባሁኑ ጊዜ ፖርቲ ሊኖረን በቻለ ነበር:: ያለው ችግር ያለው ቅራኔ ሁሉ ባልተፈጠረ፣ ወይንም እንዲቀጥል እድል ባላገኘ ነበር::” ይሉናል:: /በርዝ የተጨመረ/

በሁለቱ ቀናት ንግግሮቻቸው፣ የቀድሞው ሊቀ መንበር ያስተላለፉት መልዕክት ፀረ አብዮታዊነት ከዚህ በላይ ገለፀ ሊሆን አይችልም:: የታሰበው፣ ከውስጥ ጠላቶቻችን ጋር ታርቀን፣ ከውጭ የሚመጣ ጠላት አለ ብለን በናንጋጥጥ ከጀርባችን ሊገወጋ ነበር:: ከዚያ አልፎ ከብዙ ተጋድሎ በኋላ ያሸነፍነውን ያንድ ፖርቲ ፖሊቲካ በብሔራዊ አንድነት ስም በወርቀ ትሪ ቀረበልን::

በኛ በኩል ለነዚህ ነጥቦች ከንዲም ሁለቱ አስተያየታችንን ሰተንበታል:: ግን በይበልጥ የሚያስደስተው፣ የመኢሰማ፣ የቀበሌ ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራትና የሕዝብ ድርጅት ጊዜአዊ ጽሕፈት ቤት ወኪሎች ያንኑ ለት ማለትም እሁዱ ባደረጉት ንግግር የሰጡት መልስ ነው::

ከውጭ ለመጣ ጠላት ሕብረት ያስፈልጋል ለተባለው የሕዝብ ድርጅት ጊዜአዊ ጽሕፈት ቤት ወኪል ሰመለስ እንዲህ ይላል::

“.....ለዚህ የኢትዮጵያ አብዮታ ውያን አጭርና የማያወላውል መልስ አላቸው:: ይጠውም አብዮታችንን ከውጭ ጠላቶች ጥቃት ለማዳን አስቀድሞ የውስጥ ጠላቶችን መደምሰስ አማራጭ የሌለው እርምጃ መሆን አለበት የሚል ነው:: .....የውጭ ጠላቶች ላይ ብቻ አተኩሮ የውስጥ ጠላቶችን ችላ ማለት አደናችን ስር ለአብዮታችን መቃብር ሲቆፈር ዝም ብሎ እንደመመልከት ይቆጠራል::” ይህንን መልዕክት የቀድሞው ሊቀ መንበር በሚገባ እንዳዳመጡት ተስፋ አናደርጋለን::

በተረፈ አንድ ፖርቲ ይቋቋም ስለተባለው፣ የሕዝብ ድርጅትም ሆነ የመኢሰማ ወኪል እንዲሁም የቀበሌ ማህበራት ወኪል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ጠላቶች የውስጥ ጠላቶቹ መሆናቸውን በሚገባ ካስገነዘቡ በኋላ፣ የሚቋቋመው ፖርቲ የወዛደሩ ፖርቲ ካልሆነ በወዛደሩ ርዕዮተ ዓለም ላይ የተመረኮዘ እንጂ ልዩነቶችን አቻችሎ በ“ተራማጆች”የሚቋቋም ብሔራዊ ፖርቲ አለመሆኑን ጠቁመዋል::

ከዚህም አልፎ የቀደሞው ሊቀ መንበር ኢህአፓ ን በተዘዋዋሪ መንገድ ለህበረት ሲጋበዙ፣ የተባሉት ወኪሎች ግን በፀረ ሕዝብነቱ አውግዘውታል:: የቀደሞው ሊቀ መንበር በደፈናው ኢምፔሪያሊዝም ለሚሉት እነዚሁ የሕዝቡ ወኪሎች ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በማለት በግልፅ አውግዘዋል::

እንግዲህ ‹‹ለቀዳሚው ንግግር ድጋፍ›› የተባለው ሰልፍ በግልፅ ተፈሪ ባንቴ፣ አለማየሁ ኩባንያ የተጋለጡበት ለመሆኑ አያጠራጥርም:: ከሰፊ ሰፊ ወኪሎች ከተደረገው ንግግርም ሌላ ሕዝቡ የያዛቸው መፈክሮች ይህንን በሚገባ አረጋግጠዋል:: ከዛም አልፎ የቀደሞው ሊቀ መንበር ንግግር ሲያደርጉ፣ ሕዝቡ አብዮታዊ አደባባይን ጥሎ መውጣቱ አጋጣሚ አይደለም::

ይህ የጥር 22 ሰልፍ ከተደረገ በኋላ በመንግሥት ደረጃ ከተሰገሰጉት ፀረ ሕዝቦች ጋር የሚደረገው ትግል ከመክረሩ የተነሳ በቅርብ ጊዜ መበጠሱ እንደማይቀር ሳይታለም የተፈታ ነበር:: በነ ተፈሪ አለማየሁ ኩባንያ ደረጃ በእሁዱ ሰልፍ አብዮታዊ ይዘት የተነሳ ድንጋጤም እንደነበር አያጠራጥርም:: ሰፊው ሕዝብ በወኪሎቹ አማካይነት ባሰማውም ድምፅ ሆነ በያዛቸው መፈክሮች አንድ እርምጃ እንደሚጠብቅ አሳይቶዋል:: የሆነው ሆኖ ከጥቂት ቆየት በኋላ ሐሙስ ጥር 26 መሆኑ ነው፣ በደርግ ውስጥ ውዝግብ እንደተነሳና እንደውም ሐሙስ ጥዋት ተኩስ በብሔራዊ ቤተ መንግሥት አካባቢ እንደተሰማ ተነገረ:: ቀደም ብሎ በእሁዱና በሐሙስ መሃል በተለይ በተማሪው ዘንድ በአብዮታውያን ተማሪዎችና በኢህአፓ ደጋፊዎች መሀል ግጭት ተፈጥሮም እንደነበር ይነገራል:: እንደውም ረቡዕ ከሰዓት በኋላ በዩኒቨርሲቲ ተደርጉ በነበረው ስብሰባ አብዮታዊ ተማሪዎች በተቀናጀት ዱላ የተነሳ የኢህአፓ ደጋፊዎች ‹‹ባንዳዎችን እንጨርሳለን››ከማለት ‹‹ባንዳዎች ሊጨርሱን ነው››ወደማለቱ አዘንብለው ነበር::

ሐሙስ ጥዋት ስለተሰማው ተኩስ ብዙ የዜና ማሰራጫዎች ብዙ የተለያዩ ዜናዎች አስተላልፈዋል:: የሆነው ሆኖ የተኩሱ ውጤት ማታ በኢትዮጵያ ሬድዮ ተላለፈ:: የቀደሞ ሊቀ መንበር ከሌሎች 6 ግብረአበሮቻቸው ላይ የሞት ቅጣት እንደተፈጸመ ተነገረ:: ቀጥሎም በደረሱ ዜናዎች በተፈጠረው ግጭት ውስጥ ሰበት አብዮታዊ መኮንንና ወታደሮች እንዲሁም አብዮታዊው ጓድ ሰናይ ልኬ መሞታቸው ተሰማ:: በማግሥቱ በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌሎች ከተሞች ይህ ነው የማይባል ሰልፍ ተደርጉ እርምጃውን በመደገፍ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ድምፁን አሰምቷል:: የዚህ ሰልፍ መልዕክት በማያጠራጥር ሁኔታ ‹‹እርምጃውን እንጠብቀው ነበር አሁንም እንደግፈዋለን››የሚል ነበር::



የተፈሪ በንቴና የግብራበሮቻቸው መገደል በማያዳግም ሁኔታ የቀደሞው ሊቀ መንበር ከጥቂት ቀን በፊት ያሰሙትን ፀረ አብዮታዊ መልዕክት ያከሸፈ እርምጃ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም:: ስለዚህም ለሰፊው ሕዝብ ድል፣ በቀደመው ሊቀ መንበር ለተጠራው ኢህአፓ ሽብር የፈጠረ እርምጃ ነበር:: ስለሆነም ለአብዮታዊ ትግሉ አንድ የወደፊት እርምጃ ነው::

ሆኖም ግን ‹‹የሰፊው ሕዝብ ድምፅ›› ቁጥር 51 በተከከለ እንዳስቀመጠው›› ይህንን ማለት ግን ከፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር የሚደረገው ትንንቅ አለቀዋል አከትምዋል ማለት እንዳይደለ ግልጽ ነው::...አሁን አብዮቱ በአድሀሪዎቹ የውስጥ አርበኞች ሊቀለበስ አይችልም ማለት እንደ ገና የጥቂት ወራት ፋታ ሊያገኝ ይቻላል ማለት ብቻ ነው››

ይህ አብዮታዊ እርምጃ በፀረ ሕዝብ ሰርጎ ገቦች ላይ የተገኘ አንድ ድል የሆነውን ያህል ለሚቀጥለው ትግል አዲስ ምዕራፍ የከፈተም ርምጃ ነው:: እርግጥ የእሁዱና የአርቡ ሰልፎች ተራማጅ ድርጅቶችና ሰፊው ሕዝብ እስከ ተወሰነ ደረጃ እንደተዋሃዱ አሳይተዋል:: ከዛም አልፎ ሰፊው ሕዝብ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የመጀመሪያው ተጠያቂ መሆኑን አሳይተዋል:: ይሁንናም ገና ትግሉ መቀጠል አለበት ብዙ ነጥቦች አሁንም ያልተሟሉ አሉ:: ዝቅ ብለን እንመለከታለን:: የሆነው ቢሆን የተረጋገጠው አንዱ ሃቅ አለ:: ከእንግዲህ በተራማጆች ላይ የነፍስ ግድያ ቢፈጸም፣ በየአቅጣጫው አሻጥሮች ቢጠነሰሱ ወዘተ... የኢትዮጵያ አብዮት የወደፊት ገስጋሹ የሰፊው ሕዝብ ጉዳይ ሆንዋል::

እንደውም ከእንግዲህ በተራማጆች ላይ ግድያ ይቀጥላል ለማለት አይቻልም:: ጓድ ቴዎድሮስ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ሊቀ መንበር የተገደለው ከቶለበባው መከራ መከሸፍ ወዲህ ነው:: ጓድ ቴዎድሮስ የቀብር ስነ ሥርዓት ላይ ተራማጅ ኃይሎች በሙሉ ያሰሙት ድምፅ የአብዮቱ ሰፈር ፀረ ሕዝቦችን ለመቋቋም አሁንም በይበልጥ መጠንከር እንዳለበት እንጂ ትግሉ ማከተሙን አይደለም:: ለወደፊትም ቢሆን ይህ ግድያ ሊቀጥል ይችላል:: አብዮታዊያንም ለአብዮቱ ዱላ መምታት ይታገሉ እንጂ በተፈፀሙት ግድያዎች እንዳለበረገጉ ሁሉ፣ ለወደፊትም ለሚመጡት ግድያዎች መዘጋጀት እንጂ አይበረገግም:: እስከሁን የሚታዩትን ጉድለቶች ለማሟላት ይታገላሉ::

## 5. ከተፈሪ ባንቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መከሸፍ እስከ ጊዜአዊ ሁኔታ

ከፍ ብለን የተነተናቸው የትግል ምዕራፎች ያሳዩን አንዱ ሃቅ አለ:: እርሱም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እየወደቀ እየተነሳም ቢሆን እያደገ መሄዱንና፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እያደገ በሄደ ቁጥር ፀረ ሕዝብ ኃይሎች የትግል ዘዴያቸውን ከሁኔታው ጋር እያዛመዱ መምጣታቸውን ነው:: ባጠቃላይ ለመረዳት የምንችለው በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና በፀረ ሕዝብ ማህል የሚካሄደው ትግል ከጊዜ ወደጊዜ የተደራጀ መልክ መያዙንና ረቀቅነቱም በዚያው ያህል እየጨመረ መሄዱን ነው:: በአገራችን ሕዝባዊ ሥርዓት በነፃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ አመፅ እስከለ ተመሰረተ ድረስና እስካሁን ያለ ተደመሰሰው ፀረ ሕዝብ የመንግሥት መዋቅር እስኪል ተደመሰሰ ድረስ ደግሞ ለብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት የምናደርገው ትግል አያከትምም:: ይህን ዓላማ ምንጊዜም ባንዘነጋ ለያንዳንዱ ተጨባጭ ሁኔታ አስፈላጊውን ትንተናና የትግል ዘዴ እንደተከተልን ሁሉ ለወደፊትም መቀጠል ይኖርብናል ማለት ነው::

ከፍ ብለን እንዳስቀመጥነው፤ የነተፈሪ ባንቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መከሸፍ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ከፍተኛ ድል ቢሆንም ቅሉ፤ የኢትዮጵያን ሕዝቦች የነፃነት ትግል ከፍጻሜ አላደረሰውም::

በእርግጥ ከዛን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል አዳዲስ ድሎች ተቀዳጅተዋል:: ባንድ በኩል በሰፊው ሕዝብ ወገኖች በኩል ጥንካሬ በበለጠና ትጋት፤ ወይም በሌላ አነጋገር ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት መሸጋገር ታይተዋል:: ለምሳሌ በፀረ ሕዝቡ በኩል በተቀነባበረ የሚካሄደውን ነጭ ሽብር ለመቋቋም ተራማጆች በቀይ ሽብር ለመመከት በየፊናው አብዮታዊና ነፃ እርምጃ በመውሰድ ላይ ናቸው:: ይህም አብዮታውያን በሰፊው የሚሳተፉበት አብዮታዊ እንቅስቃሴ "አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ" ለሚለው አነጋገር አብዮታዊ ትርጉም የሚሰጠው እንቅስቃሴ ነው:: እንደምናየው ከሆነ በአብዮታውያን የተጀመረው ቀይ ሽብር በሁለት መልክ ይካሄዳል:: አንደኛው በመንግሥት የታወቀ በተለይ በቀበሌ ማህበራት ተሳታፊነት የሚካሄድ አሰሳ አለ:: በዚህም አሰሳ አብዮታውያን በሰፊው የሚሳተፉ ይመስላል:: በሁለተኛ ደረጃ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ተራማጆች በፀረ አብዮተኞች ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች አሉ:: ለምሳሌ በትምህርት ቤት በወሎ ተራማጅ ተማሪዎች የወሰዱት እርምጃ እንዲሁም ደግሞ በድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሠራተኞች ያካሄዱት ትግል ይህንን የመሰሉ ነፃ እርምጃዎች እየተስፋፉ ለመሄዳቸው ጥሩ ምስክሮች ናቸው::



ይህም የሚያሳየው የአብዮቱ ሰፈር ራሱን በመጠኑም ቢሆን እያጠናከረ መሄዱን ነው::

በወር ድርጅቶችን በሚመለከተው በኩል በተለይ ከመስከረም 12 ጀምሮ የታየው መጠናከርና በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ከነ ተፈሪ ባንቱ የቀለበሳ ሙከራ መከሸፍ በኋላ ቀጥሏል:: ምናልባት ከዛን ጊዜ በኋላ ትግሉ አመቺ ሁኔታን ስለፈጠረ ይህ አዝማሚያ በይበልጥ በተፋጠነ ሁኔታ ተካሄደ ይሆናል::

ለማንኛውም በነዚህ በወር ድርጅቶች ዘንድ አንዳንድ ተጨባጭ እርምጃዎች ታይተዋል:: አንደኛውና ምናልባትም ከፍተኛው፤ በመኢሶን ማሌሪድ ኢጭአት ሊግና ሰደድ በህብረት የወጣው መርሃ ግብር ነው:: ይህ መርሃ ግብር በሚገባ ያሳየን ነገር ቢኖር፤ የኢትዮጵያ ተራማጆች የወዛደሩን ፓርቲ መፍጠር አስፈላጊነት እንደተረዱ፤ ይህንንም ፓርቲ በጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንባት እቅዱ እንዳላቸው ነው:: ዝቅ ብለን በሰፊው እንመለስበታለን::

በተጨማሪ በዚሁ ሰሞን በመንግሥት ደረጃ አንዳንድ ለአብዮቱ አመቺ ሁኔታ የፈጠሩ እርምጃዎች ተወስደዋል:: የነዚህ እርምጃዎች መወሰድ በርግጥ በነአለማየሁና ሞገስ በሚወከለው የደርጉ ቀኝ ክንፍ መደምሰስ ጋር የተያያዘ ነው:: ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በኋላ የተወሰዱት እርምጃዎች በደርጉ እንዳይወሰዱ እነ አለማየሁ እንቅፋት ሆነው እንደነበር ለመገመት አያስቸግርም:: የሆነው ሆኖ ከተወሰዱት ተራማጅ እርምጃዎች ቢያንስ ሁለት መጥቀስ ይቻላል:: ባንዱ በኩል ሕዝቡን በማስታጠቅ ደረጃ በጥቂቱም ቢሆን በደርግ በኩል ጥረት ተደርገዋል:: በሌላ በኩል አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ላይ ጠበቅ ያሉ እርምጃዎች ተወስደዋል:: ለምሳሌ አምስት ያሜሪካን የስለላ ድርጅቶች ተዘግተው ወደ 200 የሚገመቱ የነዚህ "መሰሪያ ቤቶች" ተቀጣሪዎች ከአገሪቱ ተባረዋል:: ይህም ለአብዮቱ የማይናቅ ድል ነው::

እንግዲህ ከነ ተፈሪ ባንቱ መገደል በኋላ ባጠቃላይ ሲታይ አመቺ ሁኔታ አለ ማለት ነው::

ይህ ሆኖ ሳለ ግን አሁንም ቢሆን በፀረ ሕዝቡ በተለይ በቢሮክራሲው በኩል አሰፍቶ ባይ ተጋዳይነት አላቆመም::

ምንም እንኳን በገጠር በኢደህ ሰራዊቶች ላይ በገበሬ ማህበራት ጥብቅ እርምጃዎች ቢወሰዱም የባላባቱ መፍጨርጨር አላከተም::

ቢሮክራሲው ውስጥ የመሸጉ እንደነ ተስፋዬ ታደሰና ከፍሉ ወዳጆ ያሉ የታወቁ ፀረ ሕዝቦች ከስልጣን ቢገለሉም ቢሮክራሲው አሁንም ስልጣን ይካፈላሉ::

እንዲውም በደርግ በኩል ወደ ቢሮክራሲው ጠጋ ጠጋ ማለት ይታያል:: ለምሳሌ በቅርቡ የተሰጡት ሹመቶች ለዚህ ሁኔታ ምስክሮች ናቸው:: ከዚም አልፍ የቢሮክራሲው ተፅኖ አሳከተመም:: በከተሞች ተጀምሮ የነበረውን የአሰሳ ዘመቻ ያስቆሙት እነዚሁ የቢሮ ከበርቴዎች ናቸው:: ሰሞኑን በሚዘጋጀው ዘመቻ ቢሮክራሲው ተፅኖ ያደርጋል:: ኢህአፖ አሁንም ቢሆን ግድያውን ቀጥለዋል:: የኤርትራን ግንባሮች በሚመለከተው በኩል ኢ.ኤል.ኤፍም ሆነ ፒ.ኤል.ኤፍ አሁንም እያጠቃ ነው::

ከነ ተፈሪ በንቲ መደምሰስ በኋላ የታየው ሌላ አዲስ ሁኔታ የሶቪየት ህብረት የኩባና የምሥራቅ አውሮፖ አገሮች ከኢትዮጵያ ጋር መቀራረባቸው ነው::

ይህ ሁኔታ በደርጉ ሊቀ መንበር ወደ ሞስኮ መሄዱ ወይም ደግሞ የምሥራቅ አገሮችና የኩባ ልዑካን በበዛት ወደ አገራችን መመላለስ ብቻ ሳይሆን በለዩ ለዩ መስኮች የተገነዘበ ነው ነው::

ባንዱ በኩል በፕሮፖጋንዳ ደረጃ የነዚህ አገር ጋዜጦችም ሆኑ በነሱ ቁጥጥር ስር ያሉ ጋዜጦች ኢትዮጵያን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ማመገስ ጀምረዋል:: አንዳንዷም በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ሶሺያሊዝምን ሊገነባ እንደሚችል እስከመጻፍ ደርሰዋል:: ''አፍሪክ አዚ'' የተባለውን ጋዜጣ ብንወስዱ የኢትዮጵያን አብዮት ሲያጥላላና ኢህአፖን ሲደግፍ የነበረ ጋዜጣ ፊደል ካስትሮ ኢትዮጵያን ከጐበኙ ወዲህ አቋሙን ቀይሮ ደርግን ማመገስ ጀምሯል::

በሌላ በኩል በነዚህ አገሮችና በኢትዮጵያ ማህል ብዙ ውሎች ተፈርመዋል:: የተረጋገጠ ይሁን አይሁን አይታወቅ እንጂ አንዳንዱ የወሬ ምንጮች ባስተላለፉት ዜና መሠረት የኩባ ወታደር አማካሪዎች ኢትዮጵያ ገብተዋል:: እንዲሁም ደግሞ የምፀዋ ወደብ ለሶቪየት ህብረት የጦር መርከቦች 'ፋሲሊቲ' ሰጥቷል የሚል ዜና አለ::

ይህ ሁኔታ በይበልጥ የታየው ከነተፈሪ በንቲ መደምሰስ በኋላ ነው:: ይሁንናም ሶቪየት ህብረት አሁንም ቢሆን በሶማሌ መንግሥት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ታካሂዳለች:: እንዲሁም ፒ.ኤል.ኤፍ፣ በተለይ ባለፈው ጉባዔው ባሳለፈው ውሳኔ፣ ከምስራቅ አገሮችና ከሶቪየት ህብረት ጋር መስማማት እንደሚፈልግ አስታውቋል:: ይህ ሆኖ ሳለ አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ መንግሥት ባንዱ በኩል የሶማሌ መንግሥትና ፒ.ኤል.ኤፍ በሌላ በኩል ኃይለኛ ቅራኔ ውስጥ ናቸው:: ይሽ ሁኔታ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ለወደፊትስ አዝማሚያው ወዴት ነው? ይህንን ታሪክ ይመልሰዋል::



የሆነው ሆኖ አብዮታውያን በነቃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ አመፅ የሚታገሉላት ሕዝባዊት ኢትዮጵያ ነፃና ራስዋን የቻለች ስለምትሆን፣ ዛሬም እንደትላንት ነገም እንደዛሬ፣ አብዮታውያን ብሔራዊ ነፃነታቸውን አስከብረው ራሳቸው በራሳቸው ቸለው የአብዮትን ለመቀለበስ የሚፈልጉትን አንቀፋቶች እየደመሰሱ ወደፊት መጓዛቸው አይቀርም::

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንቀፋቶች ኢትዮጵያን መልሰው ወደ ጭለማ ሊከትዋት የተነሱት የባላባት ኃይሎች፣ ቢሮክራሲውና የቀኙ ክንፍ ንዑስ ከበርቴዎች ናቸው:: ደርግን በሚመለከተው በኩል ወደ ቢሮክራሲው በተጠጋ ቁጥር ለኢትዮጵያ ሕዝቦች እንቀፋት ይሆናልና የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ይታገሉታል::

በተለይ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ደርግ፣ በቢሮክራሲው አንፃር የሚኖረው አቋም፣ ሰሞኑን በሚዘጋጀው ዘመቻ የቢሮክራሲውን ተፅኖና መደገፉ ወይም መታገሉ፣ ባሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ከምን ጊዜም ይበልጥ፣ የሚያስፈልገውን የዲሞክራቲክ መብቶች ማወጅ አለማወጁ፣ እንዲሁም ደግሞ በእናት አገራችን ብሔራዊ ነፃነት አንፃር የሚኖረው አቋም፣ የደርግን ፀረ ሕዝብነት ወይም የሕዝብ ወገንነት ይወስናሉ::

ዛሬ በደረስንበት ደረጃ የቀረበው አማራጭ ግልጸ ነው:: ወይ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ከዚህ በፊት እንዳደረገው እስከ ተወሰነ ደረጃም ቢሆን በሰፊው ሕዝብ ጠላቶች ላይ ይዘምታል፣ ብሎም ለተራማጅ ኃይሎች መጠናከር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል:: ይህም ከሆነ በሰፊው ሕዝብና በደርግ ማህል ያለው ቅራኔ በሁለተኛ ደረጃ እንደተቀመጠ ይቀያል፣ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለሕዝባዊት ኢትዮጵያ የጀመሩትን ትግል ቀጥለው ይጓዛሉ:: ወይም ደግሞ ደርግ ከቢሮክራሲው ጋር መታረቅና መደላደልን ይመርጣል ስለሆነም አገራችንን ለውጭ ኃይሎች ይሸጣታል፣ ይህ ከሆነ ደግሞ ተራማጆችና ሰፊው ሕዝብ አፈሙዛቸውን በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ላይ ያዞራሉ፣ ለሕዝባዊት ኢትዮጵያ የጀመሩትን ትግል ቀጥለው ድል መቀዳጀታቸው ደግሞ አይቀርም::

የሚቀጥሉት ወራት ለዚህ ምርጫ የማያወላውል መልስ እንደሚሰጡ ግልፅ ነው::

## III. የት ደርሰናል ? የጊዜው የተራማጆች ተግባር ምን መሆን አለበት::

ባለፉት ክፍሎች ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሰባት ዓመት ትግል አካሄዱ በቅደም ተከተል ለመመልከት ሞክረናል:: ለመጪው ትግል ምን ማድረግ አለብን የሚለው ጥያቄ የምንመልሰው ከዚህ ትንተና ተነስተን ነው:: አስቀድመን ግን ባሁኑ ወቅት የደረስንበትን የትግል ደረጃ እስካሁን ያሟላናቸውንና ጉድለቶቻችንን ባጭሩ እንጠቁም::

ባጠቃላይ ደረጃ ስናየው በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአብዮት ሰፈርና የፀረ አብዮት ሰፈር መልኩን እየለየ መጥቷል::

የፀረ አብዮቱን ሰፈር በሚመለከተው በኩል፣ በነ አለማየሁ ተፈሪ የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍ ከተመታ በኋላ ዛሬ እንደገና ለማንሰራራት ጥረት ያደርጋል:: ባንዱ በኩል በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጥላ ስር ያሉት ፀረ አብዮት ኃይሎች በተለይ በገጠር የሚያካሂዱትን "የጦር ትግል" በማፋፋም ላይ ናቸው:: ይህ ሁኔታ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ በግልጽ ይታያል:: በሌላ በኩል በደርግ ውስጥ ያሉ አድሃሪ ኃይሎች አሁንም ከቢሮክራሲው ጋር ለመታረቅና የንዑስ ከበርቴውን ሶሺያሊዝም እንደገና ለማደላደል ጥረት ያደርጋሉ::

ወጣም ወረደም፣ እነዚህን የፀረ አብዮት ኃይሎች የሚያገናኛቸው፣ የአብዮታዊ እንቅስቃሴውን ለማደናቀፍ የሚያደርጉት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረጋቸው ነው:: ማለትም፣ ቢሮክራሲውን ማጠናከር፣ አብዮቱን መስመር ለማስለቀቅ ከመደብ ትግል ይልቅ የጎረቤት አገሮች የርስ በርስ ጦርነት ማዘጋጀትና ማፋፋም ወዘተ...

እንደዚሁ የአብዮቱ ሰፈር ራሱን በመሰብሰብ ላይ ነው:: ወዛደሩ የሙያ ማህበሩን በማጠናከር ላይ ይገኛል:: የገበሬ ማህበራት በአገር አቀፍ ደረጃ ለመደራጀት ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው:: የገበሬ ማህበራትና የወዛደሩ የሙያ ማህበሮች በብዙ ቦታ የትግል አንድነታቸውን በመገንባት ላይ ይገኛሉ:: ተራማጅና አብዮታዊ ድርጅቶች የሁለተኛ ደረጃ ልዩነቶቻቸው ላይ በመወያየት ለአንድነት ይታገላሉ:: ዛሬ አምስት ድርጅቶች የጋራ መርሃ ግብር አውጥተዋል::



እንግዲህ የፀረ አብዮትና የአብዮት ሰፈር እየተለዩና እየጠራ መምጣት የመጪውን ትግል በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያወሳው አይጠረጠርም:: በሰባት ዓመት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያደረጉት ትግል፣ የጠላትና የወዳጅ ሰፈር እየተለየ በሄደ ቁጥር ትግሉ የከረረና የረቀቀ እንደሚሆን አሳይቶናል::

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ንቃት ሀሊና በየጊዜው በመጨመር ላይ ነው:: ባንዱ በኩል በሕጋዊ መንገድ በመገልገል ተራማጆች አብዮታዊ መድረክን፣ የውይይት ክበቦችን፣ የወዛደርና የአርሶ አደር ስብሰባዎችን የፖለቲካ ትምህርት ቤት አድርገዋቸዋል:: ለሰፊው ሕዝብ ንቃትና ብስለት ቀን ተቀን አብዮታውያን በግልጽ ሲታገሉ፣ ከማሃላቸው በዙዎች በፀረ ሕዝቦች ተገድለዋል:: ይሁንና የአብዮታውያን መገደል የተቀሩትን ትጋት ፍጹም ሳያናግ፣ አብዮታውያን የቅስቀሳ ተግባራቸውን በይበልጥ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ:: በጥርና በግንቦት በአዲስ አበባም ሆነ በገጠር የተደረጉት ሰልፎች የሕዝቡን የንቃት ደረጃ በሚገባ ያንፀባርቃሉ:: ተራማጅ ድርጅቶችም በሕዝቡ ዘንድ ምን ያህል ሊዋሃዱ እንደቻሉ ለመረዳት ተችለዋል::

በድርጅትም በኩል ቢሆን የማይናቅ እርምጃ ተደርጓል:: የቀበሌ ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራት በመላ ኢትዮጵያ በማበብ ላይ ናቸው:: የወዛደሩ አገር አቀፍ የሙያ ማህበር ተቋቁሟል:: ወጣቱ በየቦታው በመደራጀት ላይ ይገኛል:: ጭቁን ሴቶችም እየተደራጁ ናቸው::

ይሁንናም የወዛደሩ ፓርቲ ገና አልተቋቋመም:: ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፀረ ፊውዳል ኃይሎችን በሙሉ የሚሰበስብ ግንባር ሕዝባዊ ሠራዊት ገና አልተቋቋሙም:: አንድነታቸውን መሥርተው ከወዛደሩ መደብ ጋር ገና በሚገባ አልተዋሃዱም:: በተግባር ደረጃ ገና ብዙ ጉድለቶች ይታያሉ:: በገጠር የገበሬ ማህበራት የጥበቃ ጓድ ቢቋቋምም ገና በዙዎቹ አልታጠቁም:: ወዛደሩ በሚገባ አልታጠቀም:: የቀበሌ ማህበራት በሚገባ አልታጠቁም:: የአብዮት ጥበቃ ጓዶች ገና መቋቋማቸው ነው:: በዚህ አንፃር በመንግሥት ደረጃ ጥብቅ እርምጃ መወሰዱ የተጀመረው ገና በቅርብ ነው፣ ለዚያውም ባሁኑ ጊዜ ለዘብ ያለ ይመስላል:: ተፈሪ በንቲ ኩባንያ የሕዝቡን መታጠቅ አፍነው፣ የትጥቅ ጉዳይ ወደ ኋላ እንዲቀር አድርገዋል:: አሁን ባለንበት ደረጃ በውጭ ጠላቶች ተደግፎ በውስጥ ጠላቶች ለሚመጣ የታጠቀን ኃይል ለመከላከልና ለመደምሰስ ገና ብዙ ጉድለት አለብን::

በፀረ አብዮቱ ሠፈር ንቃት ይታያል:: ካሁኑ በፀረ ሕዝብ አመጽ የሚሳተፉት ብዙ ናቸው፣ ቀኑ ሲደርስ ለፀረ አብዮት ለመሰለፍ ቆርጠው የተነሱ ጊዜያቸውን የሚጠብቁ አድሃሪያች ቁጥራቸው የሚናቅ አይደለም:: በተለይ ጥቅሙ የተነካበት ንዑስ ከበርቴ ብዙ ነው:: በድርጅትም ቢሆን ፀረ ሕዝቦች በየፊናቸው ተደራጅተዋል:: በተጥቀ ከኢምፔሪያሊስቶች የሚያገኙት እርዳታ ከፍተኛ ነው::

እነዚህን ሃቆች በሚገባ የተረዱ ተራማጆች፣ አብዮታዊ ድርጅቶች ዛሬ አጣዳፊ ተግባራቸውን ተልመዋል፣ እየተለሙም ናቸው:: የተራማጆች ተግባር ምን መሆን አለበት ለሚለው ጥያቄ ብዙ ይጻፍለታል ይወራለታል:: ለዚህ ጥያቄ በበኩላችን መልስ ለመስጠት እንሞክራለን::

ተራማጆች ከብዙ ጊዜ ጀምረው የቀየሱት የትግል ዓላማ አላቸው:: ይህ የትግል ዓላማ ሕዝባዊት ኢትዮጵያን መመስረት፣ አድሃሪውን የመንግሥት መኪና ደምስሶ በሕዝባዊ ስርዓት መተካትና ነፃ የሆነች ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ መመስረት እንደሆነ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ያደረግነው ትግል በቂ ምስክር ነው:: ይህ ዓላማ ከግቡ ይደርስ ዘንድ የተወሰኑ ነገሮች መሟላት አለባቸው:: ስትራቴጂክ ተግባሮቻችን ናቸው::
በየጊዜው የምንወስደው እርምጃ ለዚህ ዓላማችን እርምጃ እንደመሆኑ መጠን፣ በያንዳንዱ የትግል ደረጃ አጣዳፊ ተግባሮችም አሉን:: ስትራቴጂክ ተግባሮቻችን ከፍ ብለን የጠቀስነው ዓላማ ከግቡ እንዲደርስ የምናደርጋቸው ክንጁቶች ናቸውና፣ ተደጋግሞ እንደተነገረው በሶስት ነጥብ ይከፈላሉ:: የወዛደሩን ፓርቲ መፍጠር፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፀረ ፊውዳልና ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት ያንድነት ግንባር መመስረትና ሕዝባዊ ጦር ማቋቋም:: እነዚህን ነጥቦች አንድ ባንድ ከተመለከትን በኋላ ስትራቴጂክ ተግባሮቻችንን ለማሟላት አጣዳፊና ታክቲካል ተግባሮቻችን ምን እንደሆኑ ለመጠቆም እንሞክራለን::

<u>የወዛደሩ ፓርቲ የሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ሠራዊት መፈጠር::</u>

የኢትዮጵያ ወዛደር ለብዙ ዓመታት ከፍተኛ ትግል አድርጓል:: እንደ ማንኛውም ያገራችን ጭቁን መደቦች፣ የኢትዮጵያ ወዛደር ትግል በየካቲት 66 አዲስ ምዕራፍ ውስጥ ገብትዋል:: ባለፉት ሶስት ዓመታት ውጣ ውረድ የሞላበት ትግል ቢያካሂድም፣ ባጠቃላይ ደረጃ ወደፊት ተራምዶ ዛሬ የማይናቁ ድሎችን ተቀዳጅቷል ቢባል ሃሰት አይሆንም::



በየካቲት ዋዜማ፣ ባንድ በኩል ከፀረ ሕዝቡ ስርዓት ጋር፣ በሌላ በኩል ከነበየነ ሰለሞን ከሃዲ አመራር ጋር ባደረገው ትግል፣ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ሆኖ ንጉሣዊ አገዛዝን እንደደመሰሰ ሁሉ፣ የነበየነ ሰለሞንን አመራርንም አሽቀንጥሮ ጥሏል:: ከየካቲት በኋላም የንዑስ ከበርቴው ደንቆሮ ቡድን ያሰፈረበትን ወረራ ዛሬ የኢትዮጵያ ወዛደር ድል መትቶ፣ የራሱ የሆነ ነፃ ሙያ ማህበር አቋቁሟል:: በየካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጊዜ በንዑስ ከበርቴ ርዕዮተ ዓለም ይንቀሳቀስ የነበረው የወዛደር መደብ፣ በዛሬ ጊዜ በወዛደሩ ርዕዮተ ዓለም ከሚመሩ ድርጅቶች ጋር ርዕዮተ ዓለማዊ አንድነት በመመስረት ላይና የትግሉን አመራር በመያዝ ላይ ነው:: ይሁንና ዛሬም እንደየካቲት የኢትዮጵያ ወዛደር ትግሉን የሚመራለትና የሚያቀናብርለት ፓርቲው የለውም:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ድል እንዲመታ ከተፈለገ፣ ባገራችን ሕዝባዊ ስርዓት ለመገንባት ከተፈለገ፣ ይህ ፓርቲ መቋቋምና የትግሉን አመራር በግልጽ መያዝ ይኖርበታል ያልነው ለዚሁ ነው:: ለወዛደሩ ፓርቲ መፍጠር መታገል ከዋነኛ ተግባሮቻችን አንዱ ነው ያልነውም ለዚሁ ነው:: ይህ የሚቋቋመው የወዛደር ፓርቲ ካሁኑ ጠንካራ መሠረቶች ጥለዋል ለማለት ይቻላል:: ዛሬ በኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ነን የሚሉ ብዙ ድርጅቶች አሉ:: ተከበለናና አብዮታዊ መስመር ከሚከተሉት ማህል፣ አንዳንዶቹ ባገር አቀፍ ደረጃ ተደማጭነት አትርፈዋል:: ከግላዊ ግምት ሳይሆን ከተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ ከፍተኛ ድርጅት ለመሆኑ ብዙ ምስክሮች አሉ:: የመኢሶንን ጽሑፎች ብንወስድ ከትንተናው ሆነ ከሚያነሷቸው ነጥቦች እንዲሁም ደግሞ ከሚሰጧቸው የትግል መምሪያዎች ድርጅቱ እያደገ ሄዶ የማይናቅ ተቀባይነት እንዳገኘ እንረዳለን:: ከፍ ብለን በጥር ወርና በሜይ አንዱ አገር በት የተደረጉትን ሰልፎች ይዘት በተመለከትንበት ጊዜ እነዚህ ድርጅቶች በሕዝቡ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት እንዳላቸው ለመገመት ችለናል:: ሌሎችም ድርጅቶች በየፊናቸው ከመጠናከራቸውም ሌላ በቅርብ ጊዜ ባንድነት ለመስራት የሚያደርጉት ጥረት ራሱ ሌላ አዲስ ምዕራፍ ነው:: በመኢሶንና በማሌሪድ በህብረት የሚወጣ አውነት የተባለ ጋዜጣ እንደነበር ማንም ያውቀዋል::

ከዚህም አልፎ በቅርብ በአምስት ድርጅቶች በህብረት የወጣ የጋራ መግለጫ በተባሉት ድርጅቶች ማህል የትግል አንድነት እንዲኖር በተጨባጭ ነጥቦች ላይ ስምምነት እንደተደረሰ ያሳያል:: ይህ በአምስቱ ድርጅቶች ማህል የወጣው የጋራ መግለጫ ለትግል አንድነት ጠንካራ መሠረት ስለሆነ፣ ለወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር ማለትም ለነዚህ ድርጅቶች ድርጅታዊ ውህደት አንዱ ትልቅ ምዕራፍ ነው::

እንግዲህ በዛሬው ጊዜ በኢትዮጵያ ያሉት ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች የእድገት ደረጃ ምንድነው፣ ለትብብር የሚያደርጉት ትግል የት ደርሶዋል፣ ይህ ትብብርስ በምን ማለፍ አለበት፣ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ምን መሟላት አለበት የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልገናል::

ከተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት እንደምንረዳው ከፍ ብለንም ጠቀስነዋል ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ እንዲሁም ደግሞ ማሌሪድ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል፣ የወዛደር ሊግ፣ አብዮታዊ ሰደድ የተባሉት ድርጅቶች አገር አቀፍ ድርጅቶች ሆነዋል:: ይሁንና ከእነዚህ ድርጅቶች ውጭ ሌሎች ማርክሲስት ሌኒኒስት ቡድኖች በየለየ ቦታ እንዳሉ ለመገመት ይቻላል:: ለምሳሌ ከፍ ብለን በጠቀስናቸው 5 ድርጅቶች በጋራ የወጣው መግለጫ ራሱ መደምደሚያው ላይ ለነዚህ ቡድኖች ጥሪ ያደርጋል:: ይሁንና በዛሬ ጊዜ የማይታበል ሃቅ አለ:: ከተባሉት 5 ድርጅቶች ውጭ ያሉ ቡድኖች በተወሰኑ በፍራዎች ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ለመተዋወቅ እድል ባለማግኘታቸው እንጂ ራሳቸውን የቻሉ ድርጅቶች አይመስሉም:: በሌላ በኩል በ5ቱ ታላላቅ ድርጅቶች ማህል ለትግል አንድነት ወይም ህብረት የጋራ መርህ አለ::

እንግዲህ በዛሬው ጊዜ የነዚህ የተበታተኑ ቡድኖች በየፊናቸው መጠናከር ጊዜው ያለፈበት ይመስላል:: የዛሬው ዋና የትግል መፈክር የማርክሲስት ሌኒኒስት ህብረት ነው:: ስለሆነም እነዚህ ቡድኖች ያምስቱን ድርጅቶች የህብረት መርሃ ግብር ተቀብለው ቢቻል ከአንደኛው ድርጅት ጋር መዋሃድ አለበለዚያም እስኪዋሃዱ ድረስ በመርሃ ግብሩ ስር መሰራት ይኖርባቸዋል::

አምስቱን ድርጅቶች በሚመለከተው በኩል የአንዳንዱ ድርጅት በየፊናው መጠናከር እስከዚህ ጉዳይ አይደለም:: ሆኖም ግን ድርጅቶቹ የሚያደርጉት ጥረት ራሳቸውን ከማጠናከር ይልቅ በጋራ መርሃ ግብሩ ስር የሚደረገውን ያንድነት ትግል ማፋፋም መሆን ይኖርበታል::

ይህ ከሆነ ይህ የህብረት የጋራ መርሃ ግብር ወደ ድርጅቶቹ ድርጅታዊ ውህደት ያመራል:: ማለትም ዛሬ በተቀየሰው የጋራ መርሃ ግብር ላይ በሰፈሩት ነጥቦች አካባቢ አምስቱም ድርጅቶች ትግላቸውን ካፋፋሙ፣ በማህላቸውም የሚካሄደውን የርዕዮተ ዓለም ትግል በአንድነት መንፈስ ታግለው ካካሄዱት፣ በጠንካራ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች አንድነት ላይ የተመሰረተ የወዛደር ፓርቲ ሊቋቋም ይችላል::



ይህን የርዕዮተ ዓለም ትግል ለማካሄድ እንዲቻል፣ ወይም ደግሞ ለዚህ የርዕዮተ ዓለም ክርክር ለማካሄድ ይበልጥ አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ''ዴሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ'' የሚለው መፈክር ጊዜያዊ ነው:: ይህን የትግል መፈክር ይዘን ሁላችንም መነሳት አለብን::

እንግዲህ ይህ የድርጅቶች ህብረት ድርጅታዊ ውህደትን ይወልዳል ካልን ዘንዱ ለድርጅታዊ ውህደት መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች እንመልከት:: መጀመሪያ መረዳት የሚያስፈልገው ይህ ድርጅታዊ ውህደት በቸኮላ መመስረት እንደሌለበት ነው:: ድርጅታዊ ውህደት እንዲኖር በየለየ ድርጅቶች ማህል ሙሉ የርዕዮተ ዓለም ስምምነት ያስፈልጋል:: ይህ ስምምነት የሚገኘው ደግሞ ድርጅቶቹ በህብረት በሚያካሂዱት አብዮታዊ ትግል ነው:: በዚህ የቀን ተቀን ትግላቸው አካባቢ በሚያካሂዱት የርዕዮተ ዓለም ክርክር ነው:: በዚህ አንፃር በአምስቱ ድርጅቶች የወጣው የጋራ መርሃ ግብር ለትግል ትብብርና ለድርጅቶቹ ህብረት መሆኑ፣ ይህ የጋራ መርሃ ግብር ለወደፊት ድርጅታዊ ውህደት በር የሚከፍት ያንድነት ዋዜማ እንደሆነ ድርጅቶቹ ያሰሙት ፍላጎት፣ ለመመስረት የሚፈልጉት የወዛደር ፓርቲ በጠንካራ የርዕዮተ ዓለም አንድነት ላይ የተመረኮዘ እንዲሆን እንደተስማሙ ያሳያል:: ስለዚህም ትግል ቆርጠው ለተነሱ አብዮታውያን ተልቀ ድል ነው::

ለምሳሌ በ''አብዮታዊት ኢትዮጵያ'' ቁጥር 17 ላይ የወጣ አንድ ደብዳቤ ሊያሳምነን እንደፈለገው፣ በዛሬ ጊዜ ቶሎ ''ድርጅታዊ ውህደት'' ይፈጠር የሚሉ አስተሳሰቦች አሉ:: ይህን የመሰለ አስተሳሰብ፣ በደፈናው ቢታይ ለአንድነት ከሚቆረቆሩ ሰዎች የሚወጣ ይምሰል እንጂ፣ ጠለቅ ብሎ ሲታይ፣ የድርጅታዊ ውህደቱ በጠንካራ መሰረት ላይ እንዳይገነባ በሚፈልጉ ግለሰቦች የሚመጣ አስተሳሰብ ነው::

እንግዲህ አሁን የተገኘው የጋራ መርሃ ግብር የድርጅቶቹን የትግል አንድነት እንደሚያጠነክር እውቅ ነው:: ይህ መርሃ ግብርና ቀን ተቀን በህብረት የሚካሄደው አብዮታዊ ትግል በድርጅቶቹ ማህል የርዕዮተ ዓለም ውይይትና ከዛም ስምምነት እንዲገኝ ይረዳል:: ይህም ማለት በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ድርጅታዊ ውህደት ማለትም የወዛደር ፓርቲ እንዲቋቋም ይረዳል ማለት ነው::

በዛሬ ጊዜ እነዚህ ድርጅቶችም ሆኑ ለወደፊት የሚቋቋመው የወዛደር ፓርቲ ድርጅታዊ ነፃነቱ የተጠበቀ ከሌላ ድርጅትም ሆነ ከመንግሥት ከውጭ አገር የወዛደሮች ፓርቲዎች ሆነ ከውጭ አገር መንግሥታት ተፅኖ ነፃ የሆነ ራሱን መቻል በሚለው መርህ የሚመራ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ላይ የተመረኮዘ ፓርቲ ከሆነ የኢትዮጵያን አብዮት ለመምራትና ከግቡ ለማድረስ ይችላል:: ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ግን ይህ የሚቋቋመው የወዛደር ፓርቲ ከወዛደሩ መደብ ጋር በጥብቅ የተያያዘ መሆን አለበት:: ከወዛደሩ መደብ ጋር ለመዋሃድ የሚደረገው ትግል በይበልጥ መቀጠል አለበት ማለት ነው::

የዚህን ትግል ዋና ዋና ይዘቶች ለመመልከት እንሞክር:: የወዛደሩ ሕዝባዊ ድርጅት መጠናከር በነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ማሀል መመስረት ያለበት ግንኙነትና የግንኙነቱ መጠናከር የዚህ ትግል መርህ ሃሳቦች ናቸው::

የወዛደሩ ህዝባዊ ድርጅቶች/ማለትም የሙያ ማህበር የፋብሪካ የጥበቃ ጓዶች ልዩ ልዩ የወዛደር ኮሚቴዎች/ መጠናከር የወዛደሩ መደብ የመደቡን ጥቅም እንዲረዳና የመደቡንም አንድነት እንዲመሰርት ይረዳል::. ይህም በመሆኑ ለወዛደሩ የተሰለፉ ግንባር ቀደም ድርጅቶች ለነዚህ ህዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር በትጋት መታገል ይኖርባቸዋል:: በዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ፣ መ.ኢ.ሰ.ማ.ን ለማቋቋም በተደረገው ትግል ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል:: ይህ ጥረታቸው ለወደፊት በይበልጥ መቀጠል ይኖርበታል:: ምናልባትም ዛሬ ጉድለት የሚታየው እነዚህን ህዝባዊ ድርጅቶች ለማጠንከር በሚደረገው ትግል በኩል ሳይሆን ከነዚህ ድርጅቶች በመዋሃድ ደረጃ ይመስላል:: እርግጥ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት በወዛደሩ ህዝባዊ ድርጅቶች ተዋህደዋል ወይስ አልተዋሃዱም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የያንዳንዱን ሕዝባዊ ድርጅት ሁኔታ መመርመር ስለሚጠይቅ አስቸጋሪ መሆኑ ግልፅ ነው:: ይሁንና በማርክሲስት ሌኒኒስቶችና በወዛደሩ ህዝባዊ ድርጅቶች ማሀል ያለውን መዋሃድ ለመመዘን ሌሎች መሳሪያዎች አሉ:: ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ራሳቸው ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ:: የወዛደሩ ህዝባዊ ድርጅቶችስ በየቦታው በሚወስዱዋቸው እርምጃዎች ምን ያህል ከማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ጋር መቀራረብ ይታያል::

ለምሳሌ የሰፊው ህዝብ ድምፅን ብንወስድ በዚህ በኩል አሁንም ብዙ ጉድለት እንዳለ በየጊዜው ይጠቁማል:: እንዲሁም ደግሞ የወዛደሩን የሙያ ማህበር ብንወስድ በአመራር ደረጃ ከማርክሲስቶች ሌኒኒስቶች ጋር መቀራረብ ይታይ እንጂ በሰፊው ወዛደር ደረጃ አሁንም ሙሉ መዋሃድ አይታይም::



እንግዲህ ይህን ጥያቄ ለሟሟላት የሚደረገው ትግል የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ አይነተኛ ቦታ ይይዛል ማለት ነው:: ከሰፊው ወዛደር ጋር በጥብቅ መተሳሰር ማለት ደግሞ እድል ባጋጠመ ቁጥር ከወዛደሩ ስብሰባዎች ፊት ቀርቦ ከተጨባጭ ኑሮው የራቁ ግን በአብዮታዊ ቃላት የተሞሉ ስለመደቦች ፣ ስለቅራኔ ፣ ስለሶሻሊዝም፣ ...ወዘተ.. የሚያበረዳ ከባድ ንግግሮችን ማድረግና ከዛም ወደ ሌላ የግል ስራና ኑሮ እየተደሰቱ መመለስ አይደለም:: ከሰፊው ወዛደር ጋር መተሳሰር ማለት በመሀሉ መኖር ስሜቶቹን ፍላጎቶቹን፣ችግሮቹን በሚገባ ማጥናትና በነዚያ ላይ የተመረኮዙ መፍቴዎችን ለራሱ ለሰፊው ወዛደር መልስ በመጠቀም ለነዚህ እንዲታገል አብሮት መሰለፍ ማለት ነው:: በተጨማሪ የዚህ አይነቱ መዋሃድ በባዶ ቦታና ሁኔታን በደንብ ሳይለዩ ትላልቅ "መፍትሄዎችን" ፣ እቅዶችንና አሳቦችን በከንቱ ከማቅረብ ይረዳል::

ለማጠቃለል ያህል የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች አንድነታቸውን ካጠነከሩ የሰፊ የርዕዮተዓለም ትግል በኋላ ወደ ድርጅታዊ ውህደት የሚያመሩበትን ሁኔታ ከፈጠሩ ብሎ ከወዛደሩ ህዝባዊ ድርጅቶችና ከሰፊው ወዛደር ከተሳሰሩ ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል የደም ስር የሆነውን የወዛደር ፓርቲ የሚፈጥሩበት ሁኔታ ይመጣል:: ብሎም የኢትዮጵያ ህዝቦች 90 በመቶ የሚሰበስብ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለማቋቋም የሚደረገው ትግል ይሰምራል ማለት ነው::

ይህ አብዮታዊና ህዝባዊ ግንባር ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት ሃይሎችን የሚሰበስብ እንደመሆኑ መጠን እንዲሁም ደግሞ የወዛደሩ ፓርቲ የነዚህ ሃይሎች ግንባር ቀደም ስለሆነ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር የሚደረገው ትግል የተባለውን ግንባር ለመፍጠር አንድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይሆናል:: ግን እንግዲህ ይህን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፀረ ፊውዳልና ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት ግንባር ከወዛደሩ ፓርቲ ጋር አብረው የሚመሰርቱ ልዩ ልዩ ህዝባዊ ድርጅቶች ስላሉ እነዚህም ድርጅቶች እንዲቋቋሙ መታገል የተራማጆች ተግባር ነው:: የሴቶች ድርጅት የጭቁን ብሄረሰቦች ሃይማኖቶች ...ወዘተ ድርጅቶች እንዲሁም ደግሞ የወጣቶች ድርጅት የዚህ ግንባር መሰረት ሃይሎች ናቸው:: አብዮቱ ግቡን እንዲመታ እነዚህ ድርጅቶች በወዛደሩ ፓርቲ አመራር ስር መሰለፍ ስለሚኖርባቸው ከሁሉ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ለነዚህ ድርጅቶች መቋቋም መጠናከርና መዳበር በግንባር ቀደም እንዲታገሉ ያስፈልጋል ማለት ነው::

በዚህ አገባር በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ድርጅቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ጭቁን ብሄረሰቦችን በሚመለከተው በኩል ቢያንስ ሁለት አብዮታዊ መስመር የሚከተሉ ድርጅቶች አሉ፡፡ እነሱም የአፋር ብሄራዊ ነፃ አውጪ ንቅናቄና የኦሮሞ ብሄረሰብ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ ናቸው፡፡

በወጣቶች ደረጃ እንደዚሁ በአብዮታዊ ፋና ዙሪያ ወጣቶች ተደራጅተዋል፡፡ ተራማጅ ሴቶችም በታጋይ ኢትዮጵያዊት ዙሪያ በመሰብሰብ በለት ተለት ትግሉ ተሳትፎአቸውን እየጨመሩ ናቸው፡፡ በቅርቡም የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ በሚል መጠሪያ ስም ፕሮግራማቸውን አውጥተዋል፡፡

አብዮታውያን በተለይ ደግሞ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ዛሬ ለነዚህ የለቀ ለቀ ጭቁን ህብረተሰብ ክፍሎች ድርጅቶች ሙሉ ድጋፍና ተባባሪነት ማሳየት አለባቸው፡፡ ብሎም እነዚህን ህዝባዊ ድርጅቶች በአንድ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ከወዛደሩ ፖርቲ ጋር ማስተባበር ተግባራችን ነው፡፡ለዚህም ዓላማችን ካሁኑ በነዚህ ጭቁን የህብረተሰብ ክፍሎች ትግል መሳተፍ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ የሚጠናከሩበትንና ከሚወክሉዋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በይበልጥ የሚዋሃዱበትን ሁኔታ ለመፍጠር ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መሟላት ያለበት ጥያቄ የህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት ጥያቄ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ነፃነታቸውን በመራራና በረጅም ህዝባዊ ጦርነት እንጂ በሰላም ሊቀዳጁት አይችሉም፡፡ ስለዚህም ካሁኑ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለማቋቋም መታገል አለባቸው፡፡ በዛሬይቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ የማይቀረው የመደብ ጦርነት ፀንስ እንደሚታየው ሁሉ የህዝባዊ ሠራዊቱ ፀንስም በየቦታው በማበብ ላይ ነው፡፡

እንግዲህ ጥያቄው ይህንን ፀንስ በምን መንገድ ወደተሟላ የመደብ ጦርነትና ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት መለወጥ ይቻላል፡ የሚለው ነው፡፡

ይህንን አርእስት በሌላ ፅሁፍ በሰፊው ለማተት አቅደናል ይሁንና ካሁኑ አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦችን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ካሁኑ ወቅት የአብዮታውያን የመጀመሪያ ተግባር በመላ ኢትዮጵያ በተቋቋሙት የገበሬ ማህበራትና የቀበሌ ማህበራት የጥበቃ ጓዶች ማንቃት ማደራጀትና ካሁኑ ነፃ ሰራዊት የሚሆኑበትን መንገድ መተለም ነው፡፡ ይህ ተግባር በማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ግንባር ቀደምነት ከተካሄደ ለወደፊት የሚፈጠረው የወዛደር ፖርቲ ህዝባዊ ሰራዊቱን የሚመራበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡



እንዲሁም ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ መታየት ያለበት የጊዜው የተራማጆች ተግባር ካሁኑ በመላ ኢትዮጵያ የሚካሄደውን የመደብ ጦርነት ፅንስ የበለጠ የመደብ መልክ የሚይዝበትን መንገድ መተለምና በተቻለ መጠን የወዛደሩን አመራር እንዲያገኝ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ በዚህ አገባር ሰሞኑን ስለሚዘጋጀው ዘመቻ አብዮታውያን የጠራ አስተያየት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

ይህ ዘመቻ በኢትዮጵያ ህዝቦች የመደብ ጠላቶች ላይ እስከተሰነዘረ ድረስ አብዮታዊ ይዘት ይኖረዋል፡፡ ዘመቻውም በህዝብ ለህዝብ የሚካሄድ ከሆነ በኢትዮጵያ ህዝቦች የመደብ ጠላቶች ላይ ድል የማይቀዳጅበት ምክንያት የለም፡፡

ግን እንግዲህ በመደብ ጠላቶች ላይ እንዲሰነዘር ምን መደረግ አለበት የሚሉት ጥያቄዎች ከፍተኛ ቦታ የሚይዙ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

አሁን እንደሚደረገው ዘመቻው በቢሮክራሲ የሚመራ ከሆነ ይህ ዘመቻ የመደብ ኢላማውን እንደሚስት ጥርጥር የለውም፡፡ ዘመቻው በቢሮክራሲ ይመራ ማለት ሁለት ዓመት ሙሉ በትግል የተቋቋሙት የጥበቃ ጓዶች ፀረ ህዝብ ስርዓቱን ከመደምሰስ ይልቅ ፀረ ህዝብ ስርዓቱን ያገለግሉ እንደማለት ይቆጠራል፡፡ ቢሮክራሲው ይህንን ዘመቻ ከመራ ዘመቻውን ወደ አብዮታውያን ላይ የማያዞርበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ቢቻለውም የኢትዮጵያን ህዝቦች በብሄረሰብ በኃይማኖት ወዘተ.. ከፋፍሎ ከመደብ ጦርነት ወደ ፀረ አብዮታዊ የርስ በርስ ጦርነት የማይቀይርበት ምክንያት የለም፡፡ የዚህም ሁኔታ ውጤት በማያዳግም ሁኔታ የፀረ አብዮት ሃይሎች ድል የሚቀዳጁበትና አብዮታውያን የሚሸነፉበት ሁኔታ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ይህ ዘመቻ በአብዮታውያን መመራትና የመደብ መልክ መያዝ አለበት፡፡ ይህንን ስንገነዘብ ዛሬ ተራማጅ ድርጅቶች "ቢሮክራሲው አያዝምተን ይዘመትበት" ሲሉ ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆኑ ለመገመት አያስቸግርም፡፡ በሌላ በኩል ይህ ዘመቻ በኢትዮጵያ ህዝቦች የመደብ ጠላቶች ላይ ድል እንዲቀዳጅ ከተፈለገ የሚዘምተው ሰራዊት በአብዮታውያን መመራት እንዳለበት ሁሉ በአብዮታዊ የጦር ስልት መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ሰራዊቱም ህዝባዊ ይዘት እንዲኖረው ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘመቻው የመደብ ይዘት ይኖረውና ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ አጋጣሚ በመደብ ጠላቶቹ ላይ የማይናቁ ድሎችን ይቀዳጃል፡፡ ለዘላቂ ድልም ለህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት የማይናቅ መሰረት ይጥላል ማለት ነው፡፡

ለማጠቃለል ያህል የኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ትግል ድል ይመታ ዘንድ አብዮታውያን ካሁኑ የወዝ አደሩን ለመመስረት ታጥቀው መነሳት አለባቸው፡፡ በዚህ የትግል ጉዳናቸው በሚጓዙበት ጊዜ በያንዳንዱ የትግል ደረጃ የትግል ጉዳናቸውን የሚያስምርላቸው የትግል መፈክሮችም እንዲኖሯቸው ያስፈልጋል፡፡

ከጠቅላላ ጥናታችን እንደምንገነዘበው በዛሬው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ በታች የምንዘረዝራቸው ነጥቦች ለሃቀኛ ተራማጆች አጣዳፊ ተግባሮች ናቸው ብለን እናምንባቸዋለን::

ዛሬ ቢሮክራሲውን መመንጠርና ከአድሃሪያት ማጽዳት አስፈላጊ ሆኖ ቀርቧል::አብዮታዊ እርምጃ ካልተወሰደበት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የፀረ አብዮትን መሠረት ማጠናከርና አብዮታችንን አደገኛ አዘቅት ውስጥ መጨመር ይሆናል::ያለምንም ማወላወል አድሃሪው ቢሮክራሲ ላይ አብዮታዊ እርምጃ ተወስዶ በተራማጅ አዲስ ሃይሎች እንዲተካ መታገል ይኖርብናል::ዛሬ አብዮታችን ከውስጥ ተወጥሮ፣ከውጭ ተከቦ በሚገኝበት ወቅት የሕዝቡ መደራጀትና መታጠቅ፣በሌላ የአብዮታዊ አመራር ጥያቄ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ሆኖ በሚቀርብበት ወቅት የሰፊውን ሕዝብ መጠናከርና በአብዮታዊ አመራር መታነጽ እንደጠር የሚፈሩ ሃይሎች በሙሉ ከሰፊው ሕዝብ አመራር ይልቅ የቢሮክራሲውን አመራር እንደሚሹ እሙን ነው::ይህንንም ተረድቶ ዝም ብሎ መመልከት አይቻልም::ለዚህም:—

1ኛ/ የማስታጠቅ ዘመቻ እየተፋፋመ መሄድ አለበት::ከዚህ አልፎ ሰፊው ሕዝብ በደረሰበት የትግል ደረጃ ራሱን በራሱ ለማስታጠቅ መታገል አለበት፣

2ኛ/ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተጀምሮ የነበረው የአድሃሪያት የትጥቅ ማስፈታት መቀጠል አለበት፣

3ኛ/ የውስጥና የውጭ አድሃሪ ሃይሎችን ለመቋቋም የታቀደው ዘመቻ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ሙሉ በሙሉ እንዲላቀቅና ጽኑ አብዮታዊ አመራር እንዲኖረው ያስፈልጋል::ከዚህም ጋር ለተያያዘው ለረዥሙ መራራ ትግል ሕዝቡን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፣

4ኛ/ ይህንን ትግል ደግሞ አግቡ ሊያደርሱት የሚችሉት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ራሳቸው መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል::በርግጥ የውጭ ሃይሎች ድጋፍና እርዳታ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ያስፈልገናል::ይህ ማለት ግን ለአብዮቱ መሳካት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ማለት አይደለም::የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታቸውንና ብሔራዊ ነፃነታቸውን ለመጠበቅ የሚችሉት በመጀመሪያ ደረጃ በራሳቸው ሃይል ላይ ሲተማመኑ ብቻ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታቸውን አግቡ የሚያደርሱት ትግሉ በወዝ አደሩ ፓርቲ አመራር ስር ሲገባ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም::አሁን የወዝ አደር ፓርቲ በሌለበት ወቅት የ"ተራማጆች ሕብረት"ን የፈረሙ ድርጅቶች በሙሉ ከሰፊው ሕዝብ ጋር በመቀሃድ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ባንዲራ



ከፍ አድርገው በመያዝ አብዮቱ በትክክለኛው አቅጣጫ እንዲራመድ፣የነቃ የተደራጀና የታጠቀ የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል በአብዮታዊ አመራር እንዲታነጽ ታሪክ ፊት ትልቅ ሃላፊነት አለባቸው::እነዚህ ተራማጅ ድርጅቶች በዚህ አንጻር የሚኖራቸው አቋም ወሳኝ ይሆናል::

ሕብረቱ እንዲጠናከር፣ሕብረቱን የፈጠሩ ድርጅቶች በሁለተኛ ደረጃ በሳሳቸዉ ልዩነቶች በይፋ ውይይት እንዲካሄድባቸው፣ሕዝቡን ለማስተማርና በሚገባ ለማንቀሳቀስ ከተፈለገ ደግሞ የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መለቀቅ አጣዳፊ ጥያቄ ሆኗል::

እንግዲህ በዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ የውስጥና የውጭ ጠላቶችን በሚገባ ለመቋቋምና አብዮታችንን ለማራመድ አጣዳፊ ተግባሮቻችን ሆነው የሚቀርቡት እነዚህ ጥያቄዎች ናቸው::ማንኛውም ተራማጅና ከሕዝብ ወገን ቆሚያለሁ የሚል ድርጅትና ግለሰብ እነዚህ ጥያቄዎች በተግባር እንዲውሉ መታገል አለበት::

---

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የውጭን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦሮ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጐን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያልተቋረጠውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፲ከ የትናንትም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በ<u>ታጠቅና</u> በ<u>ትግላችን</u> ስም መጠቀም ጀምረዋል፡፡ የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም <u>ታጠቅና</u> <u>ትግላችን</u> በአስር ዓመት ቀራት ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው፡፡እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወሽንገብር በመንዛት ለማፋፋም ነው፡፡ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለማገናኘም፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያልያዙ፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች <u>ማህበር</u> አባልነትን የማያመለክቱ ግን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው ··ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን ·· በሚባል ስም የታወቀው የነ አሰፋወሰን — ወንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው፡፡

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ